# የእግዚአብሔር ታማኝነት ፤

## የእኛ ተስፋ

# ዘፍጥረት 24-33

ትምህርት 1: የይስሐቅ ሚስት — አንቺ የማን ልጅ ነሽ ?

ትምህርት 2: መገለል እና መጭበርበር — ብኩርና እና በረከት

ትምህርት 3: ያዕቆብ ሸሸ — ዔሳው ያዕቆብን ጠላው

ትምህርት 4: አጭበርባሪው ተጭበረበረ — ከቤርሳቤህ እስከ ሃራን

ትምህርት 5: ያዕቆብ ወንድ ልጆች መወለድ — ከልያ ይልቅ ርብቃን ይወዳት ነበር

ትምህርት 6: ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር ታገለ — የያቦቅን ሸለቆን መሻገር

"አንተን እንዳልበድል ፤ቃልህን በልቤ ሰወርሁ"

መዝሙር 119:11

ጥናቱ የተዘጋጀው በቲንዝፓውር ፓብሊሺንግ ነው።
የቅጂ መብት © 2014 by CrossConnect Ministries.

የቅጂ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። ይህንን ጥናት ያለ ባለቤቱ ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማባዛት በህግ የተከለከለ ነው። የዚህን ጥናት ክፍል በድምጽም ሆነ በጽሁፍ ያለባለቤቱ የጽሑፍ አልያም ደግሞ የቃል ፍቃድ ሳያገኙ ጥናቱን ማባዛት በህግ ያስጠይቃል።

# ጥናቱን ስንጀምር

## መግቢያ

አሁን መጓዝ የምትጀምሩት መንገድ ቀሪውን ዘመናችሁን በሙሉ የሚለውጥ ነው፡፡ የምትሄዱበት መንገድ ለእናንተ ከዚህ በፊት ያልተለማመዳችሁት አዲስ ጎዳና ነው የሚሆነው፡፡ ግን ይህ ጉዞአችሁ በአንድ ነገር ላይ የተመረኮዘ ይሆናል፡፡ ይህም ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅ በሚኖራችሁ ፍላጎት ላይ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለህይወታችሁ የሰጠውን የተስፋ ቃል በማወቅ እና ቃሉን በማጥናት ህይወታችሁን የደስታ ህይወት አድርጉት፡፡

ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በምትከታተሉበት ወቅት በእጃችሁ ላይ እንዲኖሩ የሚገባቸው ነገሮ አሉ፡፡ እነርሱም፡

1. የዚህ ጥናት መመሪያ መጽሐፍ፡፡ የእግዚአብሔር ተስፋ ቃል የእኛ በረከታችን ነው የሚለው ማለት ነው፡፡
2. አንድ መጽሐፍ ቅዱስ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በምትገዙበት ወቅት የምትገዙት ትርጉም እነዚህን ያካተተ ቢሆን ይመከራል

   ሀ. በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ማጣቀሻ ያለው፤ በገጹ መካከል ቢሆን ይመረጣል፡፡

   ለ. በመጽሐፍ ቅዱሱ የመጨረሻ ክፍል ጥቅስ ማውጫ ያለው፡፡

   ሐ. እንዲሁ ደግሞ የተለያዩ ታሪካዊ ካርታዎችን ያካተተ ቢሆን መልካም ነው፡፡
3. አንድ እስክርቢቶ ወይንም እርሳስ፡፡
4. አንድ ማስተወሻ መያዣ ደብተር፡፡

ከላይ በተራ ቁጥር ሁለት ስር እንደተዘረዘረው አንድ ሰው እነዚህን ያሟላ መጽሐፍ ቅዱስ ገዝቶ በእጁ ከያዘ ለጥናቱ በደንብ ተዘጋጅቷል ማለት ነው፡፡ እናም ከዚህ በኋላ የሚመጡትን ጥናቶች በሙሉ በመልካም ሁኔታ ማጥናት ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ይህ ጥናት መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት የምታደርጉት የመጀመሪያ ጥናት ከሆነ፣ ከዚህ አስቀድማችሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ዳሰሳ የሚለውን ጥናት መጀመሪያ ብታጠኑት ይበልጥ ይመከራል፡፡ ይህንን ጥናት ደግሞ በእኛ ድህረ-ገጽ ውስጥ በመግባት በነፃ ማንበብም ሆነ መውሰድ ትችላላችሁ፡፡ ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ዳሰሳ የሚለውን ጥናት ማጥናታችሁ በምታገኙት እውቀት እና በምታደርጉት ጥናት ላይ መተማመን እንድትችሉ ያግዛችኋል፡፡

ግን እዚህ ጋር ልብ እንድትሉ የምንፈልገው ነገር ቢኖር የመጽሐፍ ቅዱስ ዳሰሳ የሚለውን ጥናት ማጥናታችሁ ይህንን ጥናት በሚገባ እንድትረዱ ያግዛችኋል እንጂ የግዴታ አለመሆኑን ነው። እናም አንድ ሰው ያንን ጥናት ሳያጠና ይህንን ቢጀምር ምንም የሚገጥመው ችግር አይኖርም።

ይህንን ጥናት በምታጠኑበት ወቅት አንድ በጣም የነካችሁ ክፍል ካለ በዚያ ስፍራ መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ላይ ምልክት ለማድረግም አትፍሩ። የማጥኛ መጽሐፋችሁ ስለሆነ ከዚያ በኋላ ተመልስቻሁ ለማየት ይረዳችኋል። የራሳችሁ መጽሐፍ ነውና የፈለጋችሁበት ቦታ ላይ ምልክት በማድረግ የፈለጋችሁበት ቦታ ላይ ደግሞ ማስታወሻ በመያዝ እንደሚመቻችሁ አድርጋችሁ አጥኑት። ከፈለጋችሁ ደግሞ ከላይ እንዳልነው የማስታወሻ ደብተር ገዝታችሁ በበዚያ ላይ ሃሳባችሁን ሁሉ መፃፍ ትችላላችሁ። በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ማስታወሻችሁን ጻፉበት፣ ጥያቄ የፈጠረባችሁ ነገር ካለም ምልክት አድርጉበት፣ እናም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችሁ ከየት ተነስቶ ወደ የት እየሄደ እንደሆነም ዘግቡበት።

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የተዘጋጀው እያንዳንዳችሁ በግላችሁ ማጥናት እንድትችሉ ተደርጎ ነው። እናም በስርአት ፕሮግራም አውጥታችሁ ካነበባችሁት ያለምንም ችግር ብዙ በረከትን አግኝታችሁበት መጨረስ ትችላላችሁ። እንዲሁም ደግሞ ጥናቱን በምታነቡበት ወቅት አዳዲስ ሃሳቦችን ታገኛላችሁ፣ የእናንተን የማሰላሰል እና የማሰብ አቅም የሚፈትኑ ጥያቄዎችን ታያላችሁ።

ከዚህም ባለፈ የተለያዩ ጓደኞቻችሁን ጋብዛችሁ እነዚህን ጥያቄዎች እየተወያያችሁ ብትሰሩ ብዙ ትጠቀሙበታላችሁ።

ጥናታችሁ የተባረከ እና የደስታ እንዲሆን እንመኝላችኋለን። እግዚአብሔር በቃሉ ሲናገራችሁ ተቀባይ ልቦናንን እንዲሰጣችሁ እንመኛለን። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እግዚአብሔር አባታችን በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ የገለጠውን ታላቅ ፍቅር የምንረዳበት እና በእርሱ በኩል ያገኘነውን ደስታ እና ሰላም የምንጨብጥበት እንዲሁን ምኞታችን ነው።

# ክፍል አንድ

# አንቺ የማን ልጅ ነሽ?

# ዘፍጥረት 24 — ለይስሐቅ ሚስት

---

## የትምህርት አንድ አጠቃላይ ምልከታ

**አጠቃላይ ቅኝት**

**መግቢያ**

ጥምህርት አንድ ዘፍጥረት 24

- አብርሃም ለባሪያዎቹ የሰጠው መመሪያ
- የአብርሃም አምላክ የአገልጋዮቹም አምላክ ነው
- የርብቃ ትውውቅ
- የጋብቻ ዝግጅት
- የእግዚአብሔር ታማኝነት

# የጥናት አንድ መግቢያ

አሁን አብርሃም አርጅቷል፡፡ እናም በባህላቸው መሰረት ለልጁ ለይስሐቅ ሚስት መፈለግ አለበት፡፡ በዚህ በጥናት አንድ ውስጥ አብረሃም በነበረበት ወቅት የነበረውን ባህል ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፡፡ ይህ ባህል ከእናንተ ባህል ጋር ያለውንም ተመሳሳይነት እና ልዩነት አጢኑት፡፡ አብርሃም የቃል ኪዳኑ ወራሽ የሆነውን ልጁን እንዴት እንደሚንከባከበው እና እንደሚያስብለት ልብ በሉ፡፡

ለይስሐቅ ሚስት የምትሆነው ሴት ማን ናት? ከየትስ ተፈልጋ ትገኝ ይሆን? ይስሐቅስ አባቱ መርጦ ያመጣለትን ሚስት እንዴት አድርጎ ይቀበል ይሆን? የእነዚህን ሁሉ ጥያቄዎች መልስ የምታገኙበት ታሪክ በዘፍጥረት 24 ላይ ነው ፡፡

ታሪኩን ስታነቡት በጣም የሚስብ እና በቀላሉ የሚገባ ሆኖ ነው የምታገኙት፡፡ ነገር ግን በዚህ ጥናት ውስጥ ታሪኩን አስመልክቶ የምናነሳቸው ጥያቄዎች አባት ለልጁ ያለውን ትኩረት፣ እናም ለልጁ ትሆን ዘንድ ምን አይነት ሚስትን እደመረጠ፣ የአብርሃም አገልጋዮችን ታማኝነት፣ የአብርሃም የሩቅ ዘመዶችን ትብብር፣ እናም የተወደደችው ሚስት ለባልዋ ያመጣችውን መጽናናት እንመለከታለን፡፡ ይህች ሴት ለአማችዋ ለአብርሃም ያመጣችለትን ታላቅ መጽናናት እና ደስታ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፡፡ ይህች ሴት ባልዋን ከልብ በማፍቀር ነበር ለአባቱ ታላቅ እምነት እና ደስታን የሰጠችው፡፡

አሁን ጥናታችንን እንጀምር፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳችሁን ክፈቱና በዘፍጥረት 25፡ 19 ላይ የሚገኘውን ቃል ጻፉት

____________________________________________

____________________________________________

## ክፍል 1

## *መግቢያ*

ዘፍጥረት መጽሐፍ ስለ ይስሐቅ የሚነገርን ነገር ይህን ያህል ሰፊ የሚባል አይነት አይደለም። ይስሐቅ የአብርሃም ልጅ መሆኑን፣ እንዲሁም ደግሞ እናቱ ሳራ እንደነበረች፣ እናም ከሚስቱ ከርብቃ ጋር ኖሮ ያዕቆብ እና ኤሳውን እንደወለደ እንማራለን። ይስሐቅ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባውን የቃል ኪዳን በረከት የወረሰ ልጅ ነበር።

---

አብርሃም አርጅቶ ነበር እና ከመሞቱ በፊት ለልጁ ለይስሐቅ ሚስት ሊፈልግ ተነሳ። ዘፍጥረት ሃያ አራት ላይ ርብቃ እንዴት እንደተገኘች ታሪኩን በሙሉ እናገኛለን። ታሪኩ የሚጀምረው በአብርሃም እና በዋነኛ አገልጋዩ መካከል በተደረገ ንግግር ነው። የዚህን አገልጋይ ስም አናውቀውም። ብቻ የአብርሃም አገልጋይ ተብሎ ነው የተጠቀሰው።

ግን ጉዞአችንን ከመጀመራችን በፊት ጥናታችንን የምንቀጥለው፤ 1) በመጀመሪያ የተቀመጡ ሃቆችን እንመለከታለን 2) እናም ስለእግዚአብሔር እና ስለእኛ ማንነት የምንማራቸውን ነገሮችን ልብ ብለን እንፈልጋለን 3) ከዚያም ደግሞ ይህንን የተማርነውን እውነት በህይወታችን እንድንተገብር የሚያስችሉንን ወሳኝ ጥያቄዎች እናነሳለን።

## የቤት ስራ

---

ዘፍጥረት ሃያ አራትን አንብቡት እና በማስተወሻ ደብተራችሁ ላይ ያልገባችሁን ሁኔታ፣ ባህል፣ ቃላት፣ እንዲሁም ደግሞ ሃሳብ አስፍሩ። ብቻ እናንተ ከምታውቁት እና ከምትለማመዱት ባህል እና ወግ ለየት ያለ ነገር ካጋጠማችሁ እርሱን አስፍሩት።

## መልመጃ:

---

1. በዘፍጥት 24፡35 ላይ በአብርሃም ህይወት ውስጥ እግዚአብሔር ያደረጋቸው በጎነቶች ተዘርዝረዋል። ክፍሉን ከፍታችሁ አንብቡ እና ጻፉት

   ______________________________

   ______________________________

2. ከቁጥር ሁለት እስከ አራት ባለው ክፍል ውስጥ አብርሃም ለአገልጋዩ የሰጠው የቤት ስራ ምንድን ነበር?

   ______________________________

   ______________________________

3. አገልጋዩ ሊያደረገው ቃል የገባው ነገር ምንድን ነበር?

______________________________________________

______________________________________________

# ትምህርት

ወደ ኋላ መለስ ብለን እንመልከት እና ዘፍጥረት 10፡ 15-19 ያለውን ክፍል እናንብብ፡፡ አብርሃም ለልጁ ሚስትን ለመስጠት በፈለገበት ወቅት የከነዓን ሴቶችን ለምን እንዳልፈለጋቸው እና ከእነርሱ ርቆ ሌላ ሴትን ለምን እንደፈለገ ተመልከቱ? ______________________

______________________________________________

______________________________________________

ከነዓናውያ የራሳቸውን ጣኦት የሚያመልኩ ህዝቦች ናቸው፡፡ በገዛ እጃቸው አምላካቸውን ቀርጸው ይሰሩ እና ያመልኩታል፡፡ አብርሃም ግን ሰማይ እና ምድርን የፈጠረውን እውነተኛ አምላክ ብቻ ነበር የሚያልከው፡፡ እናም እነዚህን ከነዓናውያን አንድ ቀን የአብርሃም ዘር ሙሉ በሙሉ አጥፍቶአቸው ምድሪቱን ይወርሳል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ስለከነዓናውያን ምናውቃቸው ነገሮች አሉ፡፡ ከነዓናውያን በዘፍጥረት 10፡20 መሰረት የኖር ልጅ የ _______________ ዘሮች ነበሩ፡፡ እናም ደግሞ የሃም ዘሮች ተረግመዋል፡፡ የተረገመመበት ምክንያት ደግሞ አባቱን አለማክበሩ ነው፡፡(ዘፍጥረት 9:25-27).

በዘፍጥረት ሃያ አራት መሰረት አገልጋዩ ወደ የት እንዲሄድ ነበር የተነገረው?

______________________________________________

# ክፍል 2

## መግቢያ

የአብርሃም አገልጋይ በጣም ከባድ ሃላፊነትን የሚጠይቅ የቤት ስራ ተሰጥቶታል፡፡ እናም ይህንን ሃላፊነት ለመወጣት የገባውን ቃል ከመመልክታችን በፊት አንድ የሚቀድም ጉዳይ አለ፡፡

## መልመጃ

1. በቁጥር አምስት መሰረት ባሪያው የጠየቃቸው ጥያቄዎች ምንድን ናቸው?

________________________________________________

________________________________________________

የአብርሃምስ ምላሽ ምንድን ነበር (ቁጥር 6)?

________________________________________________

የአብርሃምስ ምክንያቶች ምንድን ነበሩ (ቁትር 7)? መለስ ብላችሁ ዘፍጥረት 12:1-3. ተመልከቱ

________________________________________________

________________________________________________

# ትምህርት

እግዚአብሔር አብርሃምን ከሃገሩ ከሃራን ጠርቶ አውጥቶታል። እናም ወደ ከነአን ምድር እየመራ ወሰደው። ግን ደግሞ ከሃራን ሳይጠራው በፊት ልጅ፣ ሃገር እና ሀብት እንደሚሰጠው ቃል ገብቶለታል። እናም እግዚአብሔር ቃሉን ጠብቆ አሁን ከረጅም አመታት በኋላ መሬትም፣ ሆነ ሃብት ሰትቶታል። እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ቃል በሙሉ ፈጽሞታል እንጂ አንድም በመንገድ የቀረ አልነበረም።

አብርሃም ለአገልጋዩ እርሱ ከሃገሩ እና ከምድሩ ተለየቶ ሲወጣ አብሮት የነበረው አምላክ እግዚአብሔር ዛሬም ከአገልጋዩ ጋር አብሮት እንደሚሆን ይነግረዋል። አብርሃም ሃገሩን እና ምድሩን ለቅቆ እንዲወጣ ጥሪ ሲቀርብለት ለጥሪው ምላሽን በመስጠት ሁሉን ትቶ እንደሄደ ሁሉ ልጁም አሁን የአብረሃም አገልጋይ ሚስት እንዲፈልግለት የተባለው ይስሐቅ፤ የአብርሃም ዘርና የቃልኪዳን ልጅ ነው። በዘፍጥረት 17 ላይ በተደረገው አዲስ ኪዳን መሰረት አብርሃም አዲስ ጅማሬን ለማድረግ የተጠራ ሰው ነው።

# ማሰላሰል

አሁን በዚህ ስፍራ ይህንን ታሪክ በምናጠናበት ወቅት የተለያዩ ጥያቄዎች ወደ አዕምሮአችን ሊመጡ ይችላሉ። ሁሉንም በጥልቀት ለመመርመር ሙከራ አናደርግም፤ ነገር ግን ካሉት እውነታዎች ተነስተን ግምቶችን እንወስለን ።

አብርሃም በዚህ ስፍራ ለልጁ ሚስት ሲመርጥለት የልጁን መብቱን የተጋፋው መስሎ ይታያችኂልን? አብርሃም በህይወቱ እግዚአብሔር ምን አይነት አምላክ እንደሆን ተለማምዶ አይቶታል፡፡ እግዚአብሔር አብረሃምን በስተእርጅናው ዘመን መጥቶ ልጅን እሰጥሃለው ባለው መሰረት ይስሐቅ ተወልዶ ከዚያም ልጁ ይስሐቅን ሊሰዋ በነበረበት ተራራ ላይ እግዚአብሔር ተገኝቶ ሲያስጥለው እንመለከታለን፡፡ እናም እግዚአብሔር ለይስሐቅ እንደሚጠነቀቅለት አብርሃም አይቷል፣ ተረድቷልም፡፡ አሁንም ቢሆን አብርሃም ለይስሐቅ እግዚአብሔር ሚስትን እንደሚሰጠው ነግሮታል፡፡

1. በቁጥር ስምንት መሰረት ልጅትዋ ከአብርሃም አገልጋዮች ጋር አብራ ለመመለስ ፍቃደኛ ካልሆነች

________________________________________

________________________________________

2. በቁጥር ዘጠኝ ላይ ባሪያው ለአብርሃም የገባለት ቃል ምንድን ነበር

________________________________________

________________________________________

# ክፍል 3

## መግቢያ

የአብርሃም አገልጋይ ግመሎችን ወሰደ እና የአብርሃምን ብልጽግና ሊገልፁ ይችላሉ ያላቸውን ስጦታዎች ጭኖ ወደ ኢፍራጠስ እና ጤግረስ ወንዞች ከተማ ወደ ካራም ጉዞውን ጀመረ፡፡ ይህች ከተማ በዘመናችን ሶርያ ተብላ ጥጠራለች፡፡

## መልመጃ

1. አብርሃም አሁን አስር ግመሎችን እና የተለያዩ ስጦታዎችን አስይዞ ባሪያውን ላከው፡፡ አገልጋዩ ወደ ከተማዋ መጣ እና ግመሎችን ከከተማዋ ቅጥር ግቢ ውጭ አቆማቸው፡፡ ወደ ከተማው በሚገባበት ወቅት ምን እንደገጠመው አንብቡ እና ጻፉት፣

________________________________________

________________________________________

2. ከቁጥር አስራ ሁለት እስከ አስራ አራት የሚገኘውን ፀሎቱን በራሳችሁ አባባል ጻፉት

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

2. በፀሎቱ ውስጥ አገልጋዩ የጠየቀው ምልክት ምንድን ነበር?

______________________________________________

______________________________________________

3. ፀሎቱን ሳይጨርስ ምን ተፈጠረ (ቁጥር 15)?

______________________________________________

4. በቁጥር አስራ አምስት መሰረት ስለ ርብቃ የተረዳቸውን ነገሮች ዘርዝር።

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

5. በቁጥር አስራ ስድስት መሰረት ብላቴናይቱ እንዴት ነው የተገለጸችው?

______________________________________________

______________________________________________

6. ውሃ ካጠጣች በኋላ የሆነውን ሁሉ ጻፍ

______________________________________________

______________________________________________

## ማሰላሰል

1. ባሪያው ያቀረበው ጥያቄ በጣም አድካሚ ነው። አስር ግመሎችን ለማጠጣት ርብቃ በጣም መመላለስ ነበረባት። ወደ ውሃው ምንጭ ወርዳ እየቀዳች ያውም እስኪበቃቸው ማጠጠት እጅግ አድካሚ ተግባር ነው።
2. በቁጥር ሃያ አንድ መሰረት አገልጋዩ ምን ሲያደርግ ነበር፤ እርስዋ ግመሎችን ስታጠጣ የነበረው

ርብቃ ግመሎቹን አጠጥታ ስትጨርስ የአብርሃም አገልጋይ ምን አደረገላት?

የአብርሃም አገልጋይ  የነበረው ቅጽበታዊ ምላሽ ምን ነበር?

3. በቁጥር ሃያ ሰባት መሰረት እግዚአብሔርን ለማምለክ ምክንያት የሆኑት ነገሮች ምንድን ናቸው?

ሀ.

ለ.

# ክፍል 4

# ትምህርት

በቁጥር ሰባት እና በቁጥር ሃያ ሰባት ላይ ስለ እግዚአብሔር ታማኝነት ተደጋጋሚ ማረጋገጫ ተሰጥቶናል፡፡ እግዚአብሔር ሁልጊዜም ቢሆን ቃሉን የሚጠብቅ አምላክ ነው፡፡ በዚህ ጥናታችን ላይ የምንመለከተውም ትልቅ ነገር ቢኖር እግዚአብሔር ሁልጊዜም ቢሆን ቃሉ የማያጥፍ አምላክ መሆኑን ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ቃል ካለን ያንን ቃልኪዳኑ እንደ ተደረገ ወይንም እንደሰጠን አድርገን መቁጠር ሁላ እንችላለን፡፡

ነገር ግን ሁልጊዜም ቢሆን እግዚአብሔር የሰጠንን የተስፋ ቃል በሚገባ መረዳት መቻል አለብን፡፡ ምክንያቱም እኛ ከእግዚአብሔር የምንፈልገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ቃል የገባው ነገር አይደለምና ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች የራሳቸውን ምኞት እና ፍላጎት እንደ እግዚአብሔር የተስፋ ቃል አድርገው በመውሰድ ነገሮች ሳይሆኑ በሚቀሩበት ጊዜ እግዚአብሔር ቃሉን የማይጠብቅ አምለክ ነው ይላሉ፡፡ እግዚአብሔር ግን ሁልጊዜ ቃሉ ይጠብቃል፡፡

## መልመጃ

1. ቁጥር 28-33:  ርብቃ ወደ ቤት ሄደች እና ለቤተሰቦችዋ ሁሉ የገጠማትን ነገሮች ነገረቻቸው። የርብቃ ወንድም ላባ እህቱ የነገረቻቸውን እንግዶች ለመገናኘት ከቤት ወትቶ ወደ እነርሱ እሮጠ። ወደ ቤትም በመጡ ጊዜ ምግብ  እንዲበሉ አቀረበላቸው።
ቁጥር 34-49: ከዚያም የአብርሃም አገልጋይ ለርብቃ ቤተሰቦች አብርሃም ከላከው ጊዜ ጀምሮ ያለውን ታሪክ በሙሉ ይተርክላቸው ጀመር። በዚህ ትረካ ውስጥ ግን ተደጋግሞ የተነሳው አንድ ቁልፍ ነገር ምን ነበር?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

2. የአብርሃም አገልጋይ ቁጥር 23 እና 47 ላይ አንድ በተደጋጋሚ ሲያነሳ የነበረው ጥያቄ እዚህ ጋር በደንብ መታሰብ አለበት። አንቺ የማን ልጅ ነሽ እያለ ሁለት ጊዜ ጠይቋት ነበር። ። ይህ ጥያቄ አብርሃም በቁጥር አራት ላይ ከሰጠው መመሪያ ጋር እንዴት ይገናኛል?

______________________________________________________________________

_____________________________________________________________________

3. ከሁሉም በላይ ግን እግዚአብሔር በመልካምነቱ አብሯቸው ነበር። በዘፍጥረት 22፡ 13 ላይ እግዚአብሔር የመስዋዕቱን በግ አዘጋጅቶ ይስሃቅን ታደገው። አሁን ደግሞ በዚህ ስፍራ ለይስሐቅ ሚስትን አዘጋጀ። አሁንም እግዚአብሔር ለአብርሃም እና ለቤተሰቡ በሙሉ ምን ያህል ታማኝ እንደሆነ መመልከት እንችላለን። በቁጠር ሃምሳ እና ሃምሳ አንድ መሰረት ለዚህ ሁሉ በጎነት ያላቸው ምላሽ ምንድን ነበር?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

4. ለርብቃ እና ለቤተሰቦችዋ የተሰጠው ስጦታ የሁለቱን ቤተሰቦች ትስስር ያመላከተ ነበር። ለርብቃ የተሰጣት ስጦታ ምን ነበር?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

5.ለወንድም እና ለእናትዋ የተሰጣትስ ስጦታ ምንድን ነበር (ቁጥር 53) ?

______________________________________________________________________

ከቁጥር 54-61 ላይ ላባን እና እናትየው ርብቃን ለይስሐቅ ሚስት እንድትሆነው ለመስጠት ማዘገጃጀት ጀምረዋል። በነጋታውም የአብርሃም አገልጋይ ወደ ጌታው ርብቃን ይዞ ለመመስ ተዘጋጅቶ ነበር። እግዚአብሔር የሰጠውን ድል ይዞ ለመመስ መንገድ መጀመር ነበረበት። ግን በቁጥር ሃምሳ አምስት ላይ ቤተሰቦችዋ የነበራቸው ጥያ ምንድን ነው?

______________________________________________

6. የአብርሃም ባርያ ግን ጠንክሮ ተሟገተ። ከዚያም የርብቃ ቤተሰቦች ከአገልጋይዋ እና ከደንገ ጡርዋ ጋር አብረው ሸኙአት። በቁጥር ስልሳ ላይ ያለውን የቤተሰብችዋን ምርቃት ጻፉት:

______________________________________________

______________________________________________

7. ቁጥር 62-67 ይስሐቅ ርብቃን ሲያገኛት የሆነውን ነገር ይመልከቱ።
ሀ. ይስሐቅ የት ነበር? ምንስ እያደረገ ነው?

______________________________________________

______________________________________________

ለ. ርብቃ ይስሐቅን ስትመለከት የጠየቀችው ምንድን ነበር?

______________________________________________

______________________________________________

ሐ. የአብርሃም አገልጋዮች ይስሐቅ ጌታቸው እንደሆነ ሲነግሯት ርብቃ ምንድን ነበር ያደረገችው?

______________________________________________

______________________________________________

መ. ይስሐቅ የአልጋዮቹን ዘገባ ከሰማ በኂላ ምንድን ነው ያደረገው?

______________________________________________

______________________________________________

ሠ. ርብቃ አሁን ሚስቱ ሆናለች። እናም ይስሐቅ በጣም ወዷታል። እርስዋ ወደ እርሱ ህይወት ይዛ የመጣች እና እርሱ ቀድሞ ያልነበረው ነገር ምንድን ነው?

## ክፍል 5

ስለ እግዚአብሔር ምንድን እንማራለን? እስኪ እንደገና ዘፍጥረት ሃያ አራትን አንብቡት። እናም በምታነቡበት ወቅት ስለ እግዚአብሔር ባህሪይ እና ማንነት የተነገረባቸውን ክፍሎች አስምሩባቸው። እናም እነዚህ ጥቅሶች የሚገኙበትን ስፍራ ጻፉት።

| ቁጥር | ቃላት ወይንም አረፍተ ነገር |
| --- | --- |
| | |
| | |
| | |
| | |

በቁጥር ሃያ ሰባት ላይ እግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነ እና ሁልጊዜ ቃሉን ሊፈጽም የሚተጋ አምላክ እንደሆነ ተገልጾ እናገኛለን። የአብርሃም ባሪያ የእግዚአብሔርን ፍቅር እና ታማኝነት በአብርሃም ሕይወት ውስጥ ተመልክቷል። አሁን ደግሞ ያንን ታማኝት እርሱ እራሱ ተለማምዶታል።

## የትግበራ ጥያቄዎች

1. ታማኝነት ማለት አንድን ነገር ለማድረግ በቃላችን መሰረት መገኘታችንን የሚያረጋግጥ ቃል ነው። ታማኝነት ደግሞ መታመንን ይፈጥራል። ለምሳሌ የትዳር ቃል ኪዳን ባል እና ሚስት አንዳቸው ለሌላው ታማኝ ሆነው መኖር እንዲችሉ የሚጠይቅ ነው። እናም ይህንን ታማኝነት ባል ወይንም ሚስት በሚያፈርሱበት ጊዜ እምነት ይጠፋል። ታማኝነት ማለት ያልሆነውን ነገር ሆነን መገኘት ነው።

   ሀ. እስኪ እናንተ በታማኝነት ዙርያ ያላችሁን ልምምድ ግለጹ?

ለ. በህይወታችሁ ታማኝነትን ያስተማራችሁ ማን ነው?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ሐ. በህይወታችሁ ታማኝ ያልሆነ ሰው ገጥሞአችሁ ያውቃል? ____________________

2. በህይወታችሁ ከእግዚአብሔር ታማኝነት ጋር በተያያዘ ጉዳይ ጥያቄ ገጥሞአችሁ ያውቅ ይሆን? ስለእግዚአብሔር ታማኝነት ምንድን ነው ያሰባችሁት? ስለ እግዚአብሔር ታማኝነትስ ያላችሁ ልምምድ ምንድን ነው?

____________________________________________________________

___________________________________________________

4. በህይወታችሁ ታማኝነታችሁን ለማረጋገጥ ብላችሁ ከፍተኛ ዋጋ የከፈላችሁበት ገጠመኝ ምንድን ነው? እናስ ሌሎች በእናንተ ታማኝነት ታንጸው እና ደስተኞች ሆነው ያውቃሉ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

## ማሰላሰል

እግዚአብሔር ታማኝ ነው ስንል በማንም አስገዳጅነት አይደለም ታማኝ የሆነው። በሁለተኛ ጢሞቴዎስ ሁለት አስራ ሶስት ላይ ጳውሎስ እንደሚናገረው ጥቅሱን ጻፉት

____________________________________________________________

____________________________________________________________

እግዚአብሔር በማንነቱ ታማኝ ነው። እግዚአብሔር ታማኝ አምላክ የሆነው ደግሞ ከፍቅሩ የተነሳ ነው። ፍቅር የእርሱ ማንነት ነው። ከዚህም በላይ መጽሐፍ ቅዱስ ስለእግዚአብሔር የሚነግረን እርሱ ጻድቅ መሆኑን ነው። 1ዮሐ1፡ 8-10 ያለውን አንብቡ። ክፍሉ እንዲህ ይላል

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

እግዚአብሔር ሰው አይደለም ቃሉን አያጥፍም። ሁሌም ለቃሉ ታማኝ ነው።

# ፀሎት

እግዚአብሔር አምላክ ሆይ አንተ ለአብርሃም ታማኝ የነበርክ አምላክ ነህ። ልክ ለአብርሃም ታማኝ እንደነበርከው ሁሉ ለእኔም ታማኝ አምላክ ነህ እና አመሰግንሃለው። ግን እግዚአብሐየር ሆይ አንዳንድ ጊዜ በህይወቴ እደክማለው የአንተን ታማኝነትም ለመቀበል እቸገራለው ስለዚህ እርዳኝ። አንዳንዴም ደግሞ እኔ ቃሌን እየቀያየርኩኝ መታመን ያቅተኛል። ግን በዚህ ሁሉ ለእኔ ስላለህ ታማኝነት እና ፍቅር አመሰግንሃለሁ።

______________________________________________________________________________።

# ክፍል ሁለት

# የብኩርና መብት እና በረከት

# ዘፍጥረት 25 እና 27 — መገፋት እና መጠላት

---

**የትምህርቱ አጠቃላይ ምልከታ**

**አጠቃላይ ቅኝት**

*መግቢያ*

ትምህርት ሁለት  ዘፍጥረት 25 እና 27

- የያይዕቆብ እና የዔሳው መወለድ
- ያይዕቆብ የዔሳውን ብኩርና ወሰደ
- የእግዚአብሔር ቃልከዳን ከእኛ ጋር
- የአባት መታለል
- ይስሐቅ ያይዕቆብን ባረከው

## መግቢያ

በዘፍጥት 25 እና 27 ላይ እንደምንመለከተው በወቅቱ በነበረው ባህል እና አመለካከት መሰረት የበኩር ልጅ መሆን ሁልጊዜ አብሮት የሚመጣው በረከት አለው፡፡ይህ የበኩር ልጅነት በረከት ደግሞ የተገባው ለዚያ ሳው ነበር፡፡ በትምህርት ሁለት እንደምንለከተው ያይዕቆብ ይህንን በረከት በማታለል አጭበርብሮ ከታላቅ ወንድሙ ወሰደበት፡፡

ያይዕቆብ የኤሳውን ብኩርና እና በረከት አጭበርብሮ መውሰዱ በይስሐቅ ቤት ውስጥ ጭንቀት እና መታመስን ፈጥሯል፡፡ ይህንን ግጭት የፈጠሩትን ነገሮችን በእርጋታ ተመልከቱአቸው፡፡ የቃል ኪዳኑ ወራሽ የሆነው ቤተሰብ አሁን በዚህ ምክንያት ታምሷል፡፡ እስኪ ይህ ቤተሰብ እንዴት እንደተረበሸ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፡፡

ግን ይሄ እንዴት ሊሆን ቻለ? እግዚአብሔር ለዚህ ቤት የገባውን ቃል ኪዳን እንዴት ሊጠብቅ ቻለ? ቤቱ በብዙ ችግር እና በደል ታምሶ እያለ እግዚአብሔር ግን ቃሉን መጠበቅ ቻለ፡፡ ከዚህ የምንመለከተው እግዚአብሔር በምንም አይነት ሁኔታ ውስጥ ቃሉን የሚጠብቅ አምላክ መሆኑን ነው፡፡

እግዚአብሔር ግን ቃሉን መጠበቁን ቢቀጥልም ልጆቹ የሰሩት በደል ያፈራው ፍሬ ነበረው፡፡ እነዚህ የበደል ፍሪዎች ምንድን ናቸው? ያዕቆብ መሸሽ ብቸኛ አማራጩ ሆነ፡፡ ዔሳው የወሰደውን እርምጃ ተመልከቱ፡፡

## መግቢያ

ይስሐቅ በሚሞትበት ወቅት ልጆቹ ያይዕቆብ እና ዔሳው በእናቱ በሳራ ዋሻ ውስጥ ወስደው ቀበሩት፡፡ በዘፍጥረት 25 ላይ የይስሐቅ ታሪክ ይቀጥላል፡፡ እግዚአብሔር የሰጠው ቃል ኪዳን ዘሩ እንደ ሰማይ ክዋክብት እና እንደ ምድር አሸዋ እንዲሚበዛ ነው፡፡ ግን አብርሃም አንድ ልጅ ብቻ ወልዶ ነው የሞተው፡፡ እናም የልጁ ሚስት ደግሞ አሁን ሞተች፡፡

የቤት ስራ

ዘፍጥረት 25፡ 19 - 34 አንብቡት፡፡

## መልመጃ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የምናገኘው የይስሐቅን ታሪክ ነው፡፡ በቁጥር አስራ ዘጠኝ እና ሃያ ላይ ያለውን ታሪክ በደንብ ለመረዳት ትንሽ ጥናት ይፈልጋል፡፡ እስኪ በደንብ እንመልከተው

1. የይስሐቅ አባት ማን ነው (ቁጥር 19)? ____________________________
2. ይስሐቅ በሚያገባበት ወቅት ስንት አመቱ ነበር (ቁጥር 20)? _____________
3. ይስሐቅ ማንን ነበር ያገባው? _____________________________

    ሀ. አባትዋ ማን ነበር? _____________________________

    ለ. ወንድሞችዋስ እነማን ናቸው? _________________________________

4. ይስሐቅ ለርብቃ ፀልዮት ነበር፡፡ የፀለየበት ጉዳይ ምንድን ነው?

    _____________________

5. ለምንድን ነው የይስሐቅ ፀሎት ትልቅ ጉዳይ የሆነው?

    _________________________________________________________

6. የእግዚአብሄር የተስፋ ቃል በይስሐቅ በኩል ከሆነ የሚፈፀመው ምንድነው መሆን ያለበት ነገር?

    ____________________________________________________________________

7. እግዚአብሔር የይስሐቅን ፀሎት እንደመለሰለት አውቀናል፡፡ በቁጥር 21 እና 23 ላይ የሆነው ነገር ምንድነው?

    ____________________________________________________________________

    ___________________________________________________________________

8. ይህ ጥቅስ ስለ ርብቃ እርግዝና የሚናገረው ነገር ምንድነው (ቁጥር 22)?

    ____________________________________________________________________

    ____________________________________________________________________

## ትምህርት 1

ርብቃ መንትያ ልጆችን አርግዛለች፤እርግዝናውም አስቸጋሪ ነበር፡፡ ከክፍሉ እንደተረዳነው በማህፀኗ ውስጥ ያሉት ልጆች ይገፋፉ ነበር፡፡ እንደ ርብቃ በእርግዝናቸው ወቅት

የተቸገሩ ሰዎች የእርሷን እርግዝና የገጠማትን ሊያስረዱን ይችላሉ፡፡ በእርግዝናዋ ወቅት የገጠማት ችገር ጌታን "ይህ ለምን በእኔ ላይ ሆነ" ብላ እንድትጠይቅ አደረጋ (ቁጥር 23)?"

## መልመጃ

1. በራስህ/ሽ አገላለፅ ጌታ ለርብቃ ምን ብሎ እንደተናገራት ፅፍ/ፊr?

______________________________________________

______________________________________________

የርብቃ ህይወት የተለየ ነው፡፡ እርሷ መንታ ልጆችን አርግዛለች፡፡ በማህፀኗ ያሉት ልጆች ሁለት ህዝብ እንደሆኑ እና እንደሚከፋፈሉ ጌታ ተናግሯታል፡፡ ከእነዚህ ሁለት ህዝቦች አንዱ ከሌላኛው ይልቅ ጠንካራ ይሆናል፡፡ ታላቁ ለታናሹ ተገዢ እንደሚሆንም ተነግሯታል፡፡ ይህ ደግሞ ከባህላዊው አሰራር የተለየ ነው፡፡

2. ርብቃ የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ መንታ ወንድ ልጆችን ወለደች፡፡ በቁጥር 25 ላይ የመጀመሪያው ልጅ እንዴት ነው የተገለፀው?

______________________________________________

ማን ብለው ሰየሙት? ________________________

3. ስለ ወንድሙ አብራራ/ሪ (ቁጥር 26).

______________________________________________

______________________________________________

4. የሁለተኛው ልጅ ስም ማነው? ____________________

ዔሳው እና ያይቆብ የተወለዱት ይስሐቅ ርብቃን ከአገባት ከሃያ አመታት በኂላ ነው፡፡ ልጆቹ ሲወለዱ ይስሐቅ 60 አመት ሰው ነው፡፡

5. ቁጥር 27 እና 28 ስለ ሁለቱ ልጆች ሲያድጉ ምን እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ስለ ዔሳው ምን እንማራለን?

______________________________________________

______________________________________________

6. ስለያይቆብስ ምን እንማራለን?

______________________________________________

______________________________________________

ልጆቹ ግልፅ የሆነ ልዩነት አላቸው፡፡ አንደኛው በአባቱ የሚወደድ አዳኝ ሲሆን ሁለተኛው ደ ደግሞ በእናቱ የሚወደድ የቤት ልጅ ነው፡፡

## <u>ክፍል 2</u>

## የቤት ስራ

ዘፍጥረት 25፡ 19 — 34 ያለውን አንብብ/ቢ፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ስለልጆቹ ባህሪይ በበለጠ እንማራለን፡፡

## መልመጃ

ያይቆብ እናቱን በምግ ዝግጅት የሚረዳት ሲሆን ዔሳው ደግሞ በአደን የታወቀ ነው፡፡

1. ዔሳው ወደ ቤት ሲመጣ ሁኔታው እንዴት ነበር (ቁጥር 29)?

   ______________________________________________

2. ያይቆብ ያቀረበለት ቅድመ ሁኔታ ምን ነበር (ቁጥር 30)?

   ______________________________________________

3. ዔሳው ለጠየቀው ጥያቄ ያይቆብ ያቀረበው የመደራደሪያ ሃሳብ ምን ነበር

   ______________________________________________

## ትምህርት 3

ቁጥር 31 የሚናገረው ስለብኩርና መብት ነው፡፡ የብኩርና መብት ምንጊዜም ቀድሞ ለተወለደ ልጅ የሚገባው ነው፡፡ የዚህ የብኩርና መብት ባለቤት የሆነ ልጅ የቤተሰቡ ሃላፊ ይሆናል፡፡ ይህ የአባቱን የሆነውን የመውረስ መብት በተለምዶ እጥፍ ድርሻ በመባል ይታወቃል፡፡

በዚህ ክፊል ውስጥ ያይቆብ ብኩርናህን ስጠኝ በማለት የጠየቀው ነገር ቀላል ወይንም ትንሽ ነገርን አይደለም፡፡ ያይቆብ የጠየቀው ዔሳው በበኩር ልጅነቱ ሊያገኘው የነበረውን መብት እና ጥቅማ ጥቅሞች በሙሉ ነው፡፡ ጌታ ለርብቃ ታላቁ ለታናሹ ይገዛል ብሎ የተናገራትን አስታውሱ፡፡ ያይቆብ ያደረገው ነገር ብልጠት የተሞላበት ነው፡፡ ዔሳው ደግሞ ለዚህ ነገር ተጋላጭ እንደሆነ ያውቅ ነበር፡፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ ዔሳው ግን ያስብ የነበረው ስለ ምግብ ብቻ ነው፡፡ የብኩርናውን መብት አሳልፎ ከሚሰጥ እና ከሚሞት የቱ ይሻለው ነበር?

## መልመጃ

ከቁጥር 33 ጋር ቀጥሉ

1. ምግቡን ከመብላቱ በፊት እንዲምልለት ያይቆብ ዔሳውን ግድ አለው። ዔሳውስ ምን አደረገ?

   ______________________________________________

   መሃላው የብኩርናውን የመውረስ መብቶች በሙሉ ለያይቆብ አሳልፎ እንዲሰጠው የሚያደር ነው።

2. ከዚህ በኂላ ያይቆብ ምግቡን ለዔሳው ሰጠው (ቁጥር 34). ዔሳው ለምን ሲል ነው የብኩርና መብቱን የሸጠው?

   ______________________________________________

   ዔሳው ያደረገው ነገር ምን ያህል የጅል ስራ ነው። ያይቆብ በጣም የፈለገውን እና ዋጋ የሰጠውን ጉዳይ ዔሳው ግን በእንጀራ እና በምስር ወጥ ለወጠው።

3. ጥቅሱ የሚያበቃው ዔሳው ከበላ እና ከጠጣ በኂላ ወጥቶ ሄደ በማለት ነው። " ከዚያም ______________________________________________."

## ክፍል 3

ከዚህ ታሪክ ስለእግዚአብሄር እንማራለን፤ ይህ ታሪክ ስለብኩርና መብት በቁጥር 15 ላይ በአጭሩ የሚናገር ነው። ከዚህ በተጨማሪ ስለይስሐቅ እና ቤተሰቡ ብዙ ነገር እንማራለን። በታሪኩ ውስጥ እያዳንዱ የቤተሰብ አባል ለየትኛው ነገር ዋጋ እንደሚሰጥ፤ ለማን እንደሚያደሉ፤ እና ተፈጥሮአዊ ዝንባሌአቸው ምን እንደሆነ አይተናል። አንዱ ወላጁ ለአንዱ ልጅ ሲያደላ እንደነበርና ለአንደኛው ልጅ ሲወግን እንደነበርም ተመልክተናል። ይሁን እንጂ እግዚአብሄር ለአብረሃም ለሰጠው የተስፋ ቃል ታማኝ በመሆኑ ይህም ቤተሰብ ይህንን የተስፋ ቃል ወራሽ ነው።

እኛ መጥፎ ሰዎች ስለሆንን እግዚአብሔር በእኛ አይሰራም ብለን እናስብ ይሆናል። የእግዚአብሄር የተስፋ ቃል የሚፈፀመው የእኛን ባህሪይ መሰረት አድርጎ ነው ወይንም እግዚአብሄር ለእኛ የሚያደርግልን ነገር የሚወሰነው በእኛ ተግባር ነው ብለው ያስባሉ። እና መልካም ሰዎች ከሆንን እርሱ ይባርከናል ካልሆንን ደግሞ አይባርከንም። ከፍ ብሎ በተመለከትነው ታሪክ ውስጥ አንደኛው ወንድሙን በማታለል ተጠቃሚ ሲሆን ነው። ዔሳው በጣም ርቦት እና ምግብ አስፈልጎት ነበር። ዔሳው ጊዚያዊ ረሃቡን ለማስታገስ ሲል የብኩርና መብትና ጥቅሙን አቃልሎት ለታናሽ ወንድሙ አሳልፎ ሰጠው። ያይቆብ ይህንን አጋጣሚ

በመጠቀም የምፈልገውን የብኩርና ጥቅሞችና መብቶች ወንድሙን በማሳሳት ሲወስድ አይተናል።

የእግዚአብሄር ተግባር በእኛ ባህሪይ ላይ የተመሰረተ አይደለም። እግዚአብሄር የሚያደርግልን ስለገባልን ቃል ኪዳን ሲል ነው። እግዚአብሄር ለአብረሃም እና ለዘሩ ዘላለማዊ ቃል ኪዳን ገብቷል። እርሱ "እነርሱ መልካም ሰዎች ከሆኑ" ወይንም "እኔ ያልኩትን ከፈፀሙ" ወይንም "ቃላቸውን ከጠበቁ" ቃሌን እፈፅማለሁ አይልም። ነገር ግን እግዚአብሄር የሚያደርግልን እርሱ ስለተነገረው ብቻ ነው። እርሱ ለአብረሃም፣ ለይስሐቅ እና ለልጆቹ የገባው ቃል ኪዳን ይጠብቃል! ሁሉም ነገር የሚሆነው እርሱ ለሰዎች ሁሉ ከአለው ታላቅ ፍቅሩ የተነሳ ነው። እኛም በጥምቀት የዚሁ የተስፋ ቃል ወራሾች ነን። የተስፋ ቃሉን እንዲፈፅመው በእግዚአብሄር ላይ ሙሉ በሙሉ እንደገፋለን። ምንም እንኳን ታማኝነት የጎደለን፣ አሳቾች እና ለሌላው የተገባውን ለእኛ የምናደርግ ሰዎች ብሆንም እርሱ ግን በታማኝነት፣በእውነት እና በንፅህናው ቃሉን ይጠብቃል።

ምንም እንኳን የተገባን ባንሆንም እግዚአብሔር ሰዎችን ለማደስ በያዘው እቅድ ውስጥ ሰዎችን ያሳትፋል። እርሱ እኛ ሁላችንን ከኃጢአታችን ሊበገሮን፣ ነፃ እና ይቅር የተባለለት ህይወት እንድንኖር መርጦናል። እግዚአብሄርም የመጀመሪያ ልጅ አለው። ስሙም ኢየሱስ ነው። እርሱም እንደ በኩር ልጅነቱ ሃፊነቱን በሚገባ ተወጥቷል። የዮሐንስ ወንጌል 3፡ 16-17 ይህንን ያስታውሰናል። እነዚህን ጥቅሶች ፃፏቸው።

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

እኛ የተባረክነው ኢየሱስ የብኩርና መብቱን ስለአላቃለለ ነው። እርሱ እንደ በኩር ልጅነቱ በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ ዘላለማዊ ህይወትን ሊሰጣቸው ፈቃደኛ ሆነ። እግዚአብሄር አብ ልጁ ኢየሱስን በመጠቀም ሰዎችን ሁሉ ለማደስና ወደ መንግስቱ ለማምጣት ፈቀደ።

## ፀሎት

ጌታ ሆይ፣ እኔ እንደያይቆብ የምፈልገውን ለማግኘት ስል ሌሎችን በማታለል ተንቀሳቅሻለሁ። የእኔ ለቤሰቦቼ፣ ለጓደኞቼ፣ እና አብረውኝ ለሚሰሩ ሰዎች ሃላፊነት የጎደለው እና ታማኝነት የሌለው አካሄድ ብዙ ነገር አበላሽቷል። አንዳንድ ጊዜ ብቸኝነት እና ተስፋ መቁረጥ ይሰማኛል። ኢየሱስ ሃጢአቴን የምቀበልበትን እና የምናዘዝበትን አቅም ስጠኝ። አንተ

እኔ በእውነት እና በታማኝነት መመላለስ እንድችል አቅምን እንደምትሰጠኝ አምናለሁ። በተለይም በተቸገርኩባቸው እና አቅም በአጣሁባቸው ድካሞቼ ላይ ____________________________________________ ብርታት እና ፀጋህን ስጠኝ። ኢየሱስ አንተ የበኩር ልጅ ሆነህ የብኩርናህን መብት ያላቃለልህ ነገር ግን እኔ የሰማያዊው አባቴ የሆነውን ሁሉ እንድወርስ ስለሞትክልኝ እጅግ አድርጌ አመሰግንሃለሁ።

## ክፍል 4

## መግቢያ

በይስሐቅ ቤት ሁሉም ነገር በጥሩ ሁኔታ እየሄደ እንዳይደለ ተመልክተናል። በርብቃ ማህፀን ውስጥ ያሉት ሁለት መንትዮች ሁለት ህዝቦች እንደሚሆኑ ጌታ ገልጧል። አንዱ ልጅ ያይቆብ ተብሎ ተሰይሟል፤ ይህም ማለት እርሱ ሲያታልልና ሲያታልል ነበር። በሚቀጥሉት ጥቂት ምዕራፎች ውስጥ ያይቆብ ሲያታልል እና ሲታለል እንደነበር እንመለከታለን። በክፍል ሁለት ውስጥ ያይቆብ እንዴት በብልጠት ዔሳውን እንዳታለለውና የብኩርናውን መብት እንደወሰደ ተምረናል። በዚሁ ክፍል ውስጥ ዔሳው እንደታላቅ ልጅነቱ ለብኩርናው ዋጋ እንዳልሰጠና እንዳቃለለው ተምረናል። እርሱ የአባቶቹን አምላክ ተወና የኬጣዊንን ልጆች አገባ (ዘፍጥረት 26:34-35)፤ እራሱ እንደተመቸው መኖር ጀመረ። ይህ ተግባሩ ለአባቱና አባቱ ወክሎት ለነበረው ቤተሰብ እና የዘር ሃረግ ክብር እና ግድ የሌለው መሆኑን የሚያመለክት ነው። ይስሐቅ እግዚአብሄር ለአብረሃም የገባውን በረከቶች የነበረበት ሰው ስለሆነ ይህ ደግሞ አስፈላጊ ነው። ለአብረሃም ቃል የተገባው ሁሉ በይስሐቅ በኩል አሁን ለያይቆብ ሆኗል።

## ትምህርት

የበኩርና መብትና በረከት ከአባት ለመጀመሪያ ልጅ የሚተላለፉ ስጦታዎች ናቸው። ብኩርና ልጅ የአባቱ የሆነውን ሁሉ እንዲወርስ የሚያደርግ ነው። አባት ልጁን ሲባርክ የሚያውጃቸው ቃላት ልጁን ቀሪውን ዘመኑን ሁሉ የሚመሩት እና የሚገዙት ናቸው። በዘፍጥረት 25:29-34 ያይቆብ እንዴት የዔሳውን የብኩርና መብት እንደወሰደ ተምረናል። አሁን ደግሞ በዘፍጥረት 27 ውስጥ እርሱ እንዴት የዔሳውን በረከት እንደወሰደ እንማራለን።

## የቤት ስራ

**ዘፍጥረት** 27:1-29 አንብብ/ቢ

***መልመጃ***

እነዚህ ጥቅሶች እንመልከት እና ታሪኩ እንዴት እንደሆነ እናጥና

1. የይስሐቅ ጤንነት እንዴት ነበር (ቁጥር 1)?

____________________________________________

____________________________________________

2. ይስሐቅ በምድር ላይ ሲኖር እድሜው ውስን እንደሆነ ያውቅ ነበር። እርሱ አርጅቷል፤ደክሟልም አይኑም ታውሯል። ስለዚህ ለዔሳው በረከቱን የሚያስተላልፍበት ጊዜ እንደደረሰ አውቋል። ለዚህም ደግሞ ዔሳውን በመጥራት ሊባርከው ነው። ለዔሳው በቁጥር 3 እና 4 የሰጠው መመሪያ ምንድነው?

    ሀ.____________________________________________

    ለ.____________________________________________

    ሐ. ____________________________________________

3. ያይቆብም "ሳልሞትም____________________________አምጣልኝ" አለው።

# ትምህርት

ምንም እንኳን ይስሐቅ ዔሳው ያለበትን ሁኔታ ቢያውቅም ሊባርከው ወስኗል። ዔሳው ለእርሱ የተወደደ ልጁ ነው። እንደ አባት እና ልጅ ሁለቱም በዔሳው የአደን ግዳይ ይደሰቱ ነበር (ዘፍጥረት 25:27-28)። ይሁን እንጂ ዔሳው የአባቱን አምላክ በመተው የራሱን መንገድ ሲከተል ይታያል (ዘፍጥረት26:34)፤ ከእግዚአብሄር ቃል ኪዳን ከሌላቸው ከእስማኤልን ቤተሰብ ጋር በጋብቻ መተሳሰሩ የዚህ ማሳያ ነው (ዘፍጥረት 28:8-9)።

## <u>ክፍል 5</u>

## ***መልመጃ***

የርብቃ ተወዳጅ ልጅ ____________ ነው። እርሷም ይስሐቅ ለኤሳው የተናገረውን ሰማች። እርሷም ብትሆን ለእራስዋ ሳይሆን ለምትወደው ልጇ ለያይቆብ የይስሐቅን በረከት መውሰድ ፈለገች።

1. ኤሳው ወደ አደን ሲሄድ ርብቃ ምን አደረገች (ዘፍረት 27:6-7)?

____________________________________________

____________________________________________

2. በቁጥር 8 ላይ ለያይቆብ እንዲያደርግ የነገረችው ነገር ምንድነው?

______________________________________________

ሀ. በቁጥር 9

______________________________________________

ለ. በቁጥር 10

______________________________________________

3. ርብቃም "ለአባትህም፥________________________________ታገባለታለህ" (ዘፍጥረት 27:10) አለችው።

4. በዚህ በእናቱ እቅድ ያይቆብ አንድ ችግር እንዳለ አሰበ። እርሱን ያሳሰበው ነገር ምንድነው (ቁጥር 11 እና 12)?

______________________________________________

በግልፅ ያሳሰበው ጉዳይ አባቱን ለማታለል ሲሞክር አባቱ ከነቃበት ከመባረክ ይልቅ ሊረግመው እንደሚችል በማሰቡ ነው።

5. ርብቃ ግን ያይቆብ በርከቱን ከአባቱ እንዲቀበል እቅዷ ከከሸፈ ግን እርግማኑን ለመቀበል ቆርጣ ተነስታለች። በቁጥር 13 ላይ ምን አለች?

______________________________________________

6. ያይቆብም ለእናቱ በመታዘዝ እናት እና ልጅ አባት እና ወንድምን ለማሳሳት በእቅዱ ተስማሙ። ይስሐቅና ለማሳሳት የተጓዙበትን ረጅም መንገድ እስቲ አስተውሉት።

ሀ. ቁጥር 14

______________________________________________

ለ. ቁጥር 15

______________________________________________

ሐ. ቁጥር 16

______________________________________________

1. ከዚያም ያይቆብ ወደ አባቱ ሄደ። በቁጥር ላይ 18 ይስሐቅ መጀመሪያ የጠየቀው ጥያቄ ምንድነው? ________________________________

2. በቁጥር 19 ላይ ፤ የያይቆብ ምላሽ ምንድነው?

______________________________________________

ዔሳው ፈጥኖ በመመለሱ ይስሐቅ ገርሞታል (ቁጥር 20).

እርሱም " ______________________________________________"ጠየቀው፡፡

3. የያይቆብ ምላሽ፤ ______________________________________________

4. በቁጥር 21 ላይ ይስሐቅ ልጁ ዔሳው መሆኑን ለማረጋገጥ ወደ እርሱ እንዲጠጋና ______________________________________________ ጠየቀው፡፡ ከዚህ በፊት ተታልሎ የማያውቅ ከሆነ ለምድነው ይስሐቅ ዔሳው መሆኑን የተጠራጠረው? ስለዚህ ጉዳይ ምን ታስባለህ/ሽ?__________________________________________

ይስሐቅ የኖረው ማታለል በነበረበት ቤት ውስጥ ነው፡፡ ባለቤቱ ለምትወደው ልጇ ለያይቆብ የማይገባውን እንዲያገኝ ስለፈለገች ይስሐቅን አታለለችው፡፡ የይስሐቅ ልጅ የሆነው ያይቆብ የወንድሙን የዔሳውን የብኩርና መብት የሆነውን ለማግኘት ሲል ወንድሞን አታለለው፡፡ አሁን ደግሞ እናት እና ወንድም የአባትን በረከት ለማግኘት ሲሉ በማታለል ተግባር ተጠምደዋል፡፡

5. ምንም እንኳን ድምፁ የያይቆብን ቢመስልም የእጁ ፀጉር ግን የዔሳውን ይመስላል፡፡ በዚህም መንገድ የማታለል ተግበሩ ቀጠለ፡፡ በቁጥር 24 ላይ ይስሐቅ አንድ ጥያቄ እንደገና ጠየቀ ______________________________________________

6. ያይቆብም እንዲህ ብሎ መለሰ ______________________________________________

7. ያዘጋጀለትን ምግብ እንዲያመጣለት ይስሐቅ ነገረው፡፡ ምግቡንም በላ ወይኑንም ጠጣ፡፡ ከዚያም ያይቆብን እንዲስመው ወደ እርሱ እንዲጠጋ ጠራው፡፡ በቁጥር 27 ላይ እርሱ በእርግጥ ዔሳው እንደሆነ ይስሐቅን ያሳመነው ነገር ምድነው?

______________________________________________

8. በስተመጨረሻም ባረከው፡፡ ከቁጥር 28-29 ያለው በረከት ምንድነው?

ሀ. "የልጄ ሽታ______________________________________________::"

ለ. "እግዚአብሄር ______________________________________________::"

ሐ. "አህዛብ ______________________________________________::"

መ. "የሚረግምህ______________________________________________::"

# የግል ትግበራ

ይስሐቅ ለልጁ ለያይቆብ የሰጠው በረከት ምንድነው! ሰዎች እናንተን ባርከው ያውቃሉ? ወላጆቻችሁስ? ጓደኞቻችሁስ? ቄስ ፤ ወንጌላዊ ወይንም የቤተክርስትያን ሽማግሌስ?

በአንዳንድ ባህል ውስጥ አንዱ ሌላውን መባረክ የተለመደ ነገር አይደለም። በረከት ለተቀባዮ የተለያየ አቅሞችን ይሰጣል። እግዚአብሄር ለእናንተ ያለውን በረከት መስማት ትችላላችሁ?

1. እርሱ ምን እንዲናገራችሁ ትፈልጋላችሁ?

_______________________________________________

_______________________________________________

2. ለትዳር አጋራችሁ፣ ለልጃችሁ፣ ለስራ ባልደረቦቻችሁ ምን አይነት በረከትን መባረክ ትወዳላችሁ?

_______________________________________________

ልጅ ያደገበት ቤት ለቅቆ ሲሄድ "ልጄ አስታውስ እወድሃለሁ" ብሎ መባረክ ከወላጅ የሚጠበው ሲሆን ለልጅ ደግሞ ትልቅ በረከት ነው።

3. በዘፍጥረት 12 ላይ አብረሃም ለሌሎች በረከት እንዲሆን እግዚአብሄር ባረከው። ጊዜ ወስዳችሁ ህይወታችሁ ለሌሎች ሰዎች ህይወት እንዴት በረከት መሆን እደሚችል አስቡ። በእናንተ በኩል ህይወቱ ሊባረክ የሚችለው ሰው ወይንም ሰዎች ማን ነው ወይንም እነማን ናቸው?

_______________________________________________

_______________________________________________

4. የዚያን ሰው ህይወት ምን በማለት ወይንም ምን በማድረግ ትባርካላችሁ?

_______________________________________________

_______________________________________________

## ፀሎት

ጌታ ሆይ የእኔን ህይወት በእውነትህ ባርከሃል። አንተ እኔን አታታልለኝም። አንተ ለእኔ መልካም የሆነውን ሁሉ ታደርግልኛለህ። እኔን የሚባርቀውን ቃልህን እሰማ ዘንድ እርዳኝ፣ "የተስፋ አምላክም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተስፋ እንድትበዙ በማመናችሁ ደስታንና ሰላምን ሁሉ ይሙላባችሁ" ሮሜ 15፡13 ። የሌሎችን ህይወት የምባርክበትን አጋጣሚ ሁሉ በትጋት እወጣ ዘንድ እርዳኝ። በማደርገው ነገር ሁሉ ክብርና ምስጋናን አመጣልህ ዘንድ እርዳኝ።

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

# ትምህርት ሶስት

# ዔሳው ያይቆብን ጠላው፤ ያይቆብ ሸሸ

# ዘፍጥረት 27 እና 28

---

**የትምህርት 3 ቅኝት**

ምልከታ

መግቢያ

ትምህርት 3 ፤ ዘፍጥረት 27 እና 28

- ማታለል እና እውነት
- የያይቆብ ማታለል ተጋለጠ
- ለይቅርታ የእግዚአብሄር ታማኝነት
- ያይቆብ ወደ ካራን ምድር ሸሸ
- ማታለል ጠላትነትን አስከተለ

# መግቢያ

ማታለል ምንድነው? ከየትስ መጣ ? ማታለል የሚያስከትላቸው ነገሮች ምድናቸው? ስለማታለል መፅሐፍ ቅዱስ ም ያስተምረናል? ማታለል መጥፎ ዜና ሆነ መልካም ዜና ምንድነው? በዚህ ክፍል ውስጥ ማታለል ሊያስከትል የሚችለውን ወዳጅነትን ማበላሸትና መከፋፈል ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ገምቱ።

በትምህርት 2 ያይቆብ ወንድሙን እና አባቱን በማታለል የእረሱ ያልሆነውን በረከትን እና የብኩርና መብትን እንዳገኘ አይተናል። አሁን ደግሞ በክፍል 3 ወንድሙ እርሱን በማታለል ለእርሱ የተገባውን በረከት ከወሰደበት በኋላ ዔሳው ምን አይነት ምላሽ እንደሰጠ እናያለን። የርብቃን ምክርና የዔሳውንም ፍፃሜ እናያለን።

ክፍሉን ስናጠቃልል ጥናቱን ከግል ህይወታችን ጋር እናዛምዳለን። እኔ ከማታለል ጋር ያለኝ ግንኙነት ምን ይመስላል? አታላይ ነኝ ? ሌሎች አታልለውኝ ያውቃሉ? መፅሐፍ ቅዱስ ራሳችንን እንኳን እንደምናታልል ይነግረናል። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ብለን እንጠይቅ ይሆናል። ጊዜ ወስዳችሁ ራሳችሁን መርምሩ። ጌታ ለሚያሳያችሁ እውነተኛ ማንነታችሁ ምላሽ ስጡ።

## <u>ክፍል 1</u>

## የቤት ስራ፤ ዘፍጥረት 27 አንብቡ

# ትምህርት

ማታለልን የሚከተሉ ሌሎች ተግባራት ስለአሉ ጊዜ ወስደን ስለማታለል መፅሐፍ ቅዱስ በተለያየ ስፍራ የሚያስተምረውን እንመለከታለን። ማታለል ምንድነው? የሚያታልሉ ሰዎችን ሊከተላቸው የሚችለው ነገሮች ምንድናቸው? የማታለል መሰረታዊ ችግሮች ምንድናቸው? እነዚህን ጥያቄዎችን ለመመለስ የተለያዩ ክፍሎችን ከመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናጠናለን።

1. ማቴዎስ 13:22-23 — የሚያታልለን ነገር ምንድነው?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

2. ኤርሚያስ 17:9 — ማታለል ከየት ይመጣል?

________________________________________

3. ማርቆስ 7:20-23 — በሰው ልብ ውስጥ ምን አለ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

4. ዘሌዋዊያን19:11 — የእግዚአብሄር ትዕዛዝ ምንድነው?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

ማቴዎስ ማታለል ከብልፅግና ጋር ይመጣል ይላል፡፡ ሰዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከብልፅግና ጋር በተያያዘ በማታለል ውስጥ ይገባሉ፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ የሚፈልጉትን የግድ ማግኘት አለብኝ ብለው ስለሚያስቡ ነው፡፡ አልፎ አልፎ ደግሞ ማግኘት አለብን ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ ሰዎች የሚገልጉት ከአገኙ በኋላ የአገኙት ነገር እርካታን ወይንም ደስታን ወይንም መወደድን ያመጣልናል ብለው በማሰባቸና ይህንን በማመናቸው መታላቸውን ይገነዘባሉ፡፡ እውነቱ ግን ውሸትን በማመን መታለላችን ነው፡፡

ኤርሚያስ የሚነግረን የሰው ልብ ተንኮለኛ ክፉም እንደሆነ ነው፡፡ እርሱ የሚናገረን ልብ አታላይ እንደሆነና ፈውስም እንደሌለለው ነው፡፡ የኃጢአት መሰረታዊ ነገር ማታለል ሲሆን ሃጢአትም ወደ ሰው ልብ ይገባል፡፡ በኤደን ገነት ውስጥ እባቡ ሄዋንን በአናገራት ጊዜ የሆነውን አስቡት፡፡ እባቡ የተናገራት በሙሉ የማታለል ቃላት ነበሩ፡፡ ማርቆስ ደግሞ የሚናገረን በልብ ውስጥ ማታለል እንዳለ ነው፡፡ ልብ እንደ ኃጢአተኛ ሰውነታችን የእኛ ማንነት መገለጫ ነው፡፡

በዘሌዋዊያን ውስጥ አንዳችን አንዳችንን እንዳናታልል እግዚአብሄር አዝዞናል፡፡ እርሱ ይህን ትዕዛዝ የሚሰጠን ለእኛ ጥቅም ነው፡፡ ያይቆብ ሲያታልል ዋሽቶ ነበር፡፡ አባቱን በተደጋጋሚ ዋሸው፡፡ ሁሉም አይነት ማታለል መዋሸት ነው፡፡ መፅሐፍ ቅዱስ ሲያስተምረን ዲያብሎስ “እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት

አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና። ” ዮሐ 8፡44 በማለት የስተምረናል።

የማታለል ተቃራኒው እውነት ነው። የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከቱና ስለእውነት ተማሩ፤

1. ምሳሌ 14:5 — የታማኝ ምስክር ባህሪያት ምንድናቸው?

____________________

____________________

2. ኤፌሶን 4:21-24 — እውነት ከየት ይመጣል?

____________________

____________________

3. 1 ቆሮ 3:18 — ምንን ከማድረግ ማቆም አለብን?

____________________

____________________

4. 1 ዮሐ 1:8-9 — ይህንን ክፍል ፃፈው/ፊው

____________________

____________________

____________________

____________________

5. 1 ጴጥሮስ 2:21-22 — ክርስቶስ የተወልን መከተል ያለብን ምሳሌዎች ምንድናቸው?

____________________

____________________

____________________

6. ዮሐንስ 14:6 —ኢየሱስ ስለራሱ ምን ብሎ ተናገረ?

____________________

____________________

እውነት ማለት ማታለል አይደለም። እውነታ ይታመናል። ይስሐቅ ልጁን ከመባረኩ በፊት ለማረጋገጥ ስንት ጊዜ ጠየቀ? በቤቱ ማለል ነበር። ማየት አለመቻሉን አላማነም። እውነት እና

ማታለል አብረው መኖር አይችሉም፡፡ አንድ ሰው እውነተኛ ምስክር ነው ወይንም አታላይ ምስክር ነው መሆን የሚችለው፡፡

እውነት ከኢየሱስ ነው የሚመጣው፡፡ እውነት የእርሱ ማንነት መገለጫ ነው፡፡ ዲያብሎስ ሲዋሽን ኢየሱስ ግን እውነትን ስለሚናገረን እናምነዋለን፡፡ ከሁሉም በላይ ግን ራሳችንን መዋሸት ማቆም አለብን፡፡ ምንም ሳንሆን ያልሆነውን እንደሆንን ሆነን ስናስብ ራሳችንን እንዋሻለን፡፡ ራሳችንን እንደእጅግ አስፈላጊ፤ልዩ ችሎታ እንዳለን እና ከሌሎች የበላይ አድርገን ስናስብ ያንን ጊዜ እራሳችንን እናታልላለን፡፡ አትታለሉ፡፡ እግዚአብሄር አይዘበትበትም፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ በገላቲያ 6፡7-8 ላይ የዘራነውን ያንኑ እናጭደዋለን በማለት ይናገራል፡፡ ይህ ደግሞ የመዝራትና የማጨድ ህግ ነው፡፡ ስንዴን የሚዘራ ስንዴን ያጭዳል፡፡ በህይወታችን ውስጥ ማታለልን ስንዘራ የምናጭደው ያን ብቻ ነው፤ ማታለልን ዘርተን እውነትን ልናጭድ አንችልም፡፡

ዮሐንስ መጥፎ ዜና እና መልካም ዜናን ይነግረናል፡፡ መጥፎ ዜናው ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እንደምናታልል ሲሆን ለራሳችን ስለራሳችን እንዋሻለን፡፡ ይህንን የሚያደርጉትን ሰዎች ዮሐንስ እውነት በውስጣችሁ የለም ይላል፡፡ ይሁን እንጂ መልካም ዜና አለ፤ ይህም መልካም ዜና ደግሞ ኃጢአታችንን ብንናዘዝ እግዚአብሔር ታማኝ ስለሆነ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ታማኝ እንደሆነ ነው፡፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሳ ለአብረሃም፤ለይስሐቅና ለያይቆብ ታማኝ እንደነበር ለእኛም ኃጢአታችንን ይቅር በማለት ታማኝነታችንን ይገልፀል፡፡ ለራሳችን እና ለእርሱ እውነትን እንድንናገር እግዚአብሔር ይፈልጋል፡፡

እና በማታለል ኃጢአት በደለኞች ነን፡፡ የእኛ የማታለል ተግባር ከርብቃና ከያይቆብ የተለየ ሊሆን ይችላል ይሁን እንጂ ማታለል ማታለል ነው፤ ልዩነት የለውም፡፡ እየሱስ ወደምድር የመጣው ከሚያታልለን ነገር ሁሉ ነፃ ሊያወጣን ነው፡፡ ልባችን ያታልለናል፡፡ ዲያብሎስ ያታልለናል፡፡ አለማችን እኛን በሚያታልሉ ነገሮች የተሞላች ናት፡፡ ጓደኞቻችን እና ወላጆቻችን ያታልሉናል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በመከራውና በሞቱ እኛን ከከማኛውም ኃጢአት ነፃ አውጥቶናል፡፡ የእርሱ ምህረት እና ፀጋ እንደልጆቹና ወራሾቹ በነፃነት በመንግስቱ ውስጥ እንድንኖር አድርጎናል፡፡

## ክፍል 2

***መልመጃ፤*** ዘፍጥረት 27 እንመልከት። ያይቆብ ተባርኮ ከአባቱ ከተለየ በኋላ ዔሳው ወደ ቤት መጣ።

1. ዔሳው ምን አደረገ (ቁጥር 31)?

_______________________________________________

2. ይስሐቅ ምን ጠየቀ?

_______________________________________________

3. የዔሳው መልስ ምን ነበር?

_______________________________________________

4. የያይቆብ ማታለል ተገለጠ። የእያንዳንዱን ሰው ስሜታዊ ሁኔታን አስተውሉ።

   ሀ. የዔሳው ሁኔታ እንዴት ነበር ቁጥር 33

_______________________________________________

   ለ. የዔሳው ሁኔታ እንዴት ነበር ቁጥር 34:

_______________________________________________

5. ሁለቱም ሰዎች ተታልለዋል። ይህንን ደግሞ ያይቆብ እንዳደረገው ማመን አልቻሉም። በቁጥር 36 ላይ ዔሳው ስለ ያይቆብ ምን አለ?

_______________________________________________

_______________________________________________

6. በቁጥር 36 ላይ ዔሳው አባቱን " በረከትን ለእኔ አላስቀረኀልኝም?" ብሎ ጠየቀ። በቁጥር 37 ላይ ይስሐቅ ለዔሳው ለያይቆብ ያለውን ሁሉ እንደሰጠው ነገረውና " ለአንተ ግን ምን ላድርግልህ?" ብሎ ጠየቀው። አባቱ ምን ያህል እንደተሰማው እስኪ አስቡት። አባቱን ዔሳው በቁጥር 38 ላይ ምን ብሎ ጠየቀው?

_______________________________________________

7. ከዚያም ይስሐቅ ዔሳውን ባረከው። በቁጥር 39 እና 40 ላይ ምን አለ?

_______________________________________________

_______________________________________________

8. ይህንን እንደ በረከት ትቆጥሩታላችሁ? ዔሳው የተባረከበትን በረከትንና ያይቆብ የተባረከበትን በረከታ አነፃፅሩት።

_______________________________________________

## ማሰላሰል

አሁን የጀመርነውን ታሪክ ልናጠቃልል ነው። በቤተሰቡ ውስጥ ማታለል ሰፍኝዋል፤ አባትም ልጁን ባርኮታል። ጌታ ለርብቃ ታላቁ ለታናሹ ይገዛል ሲል ይህንን አይቶ ይሆንን?

1. ርብቃና ያይቆብ በዚህ የማታለል ተግባር ውስጥ ባይገቡ ኖሮ ታሪኩ ምን ሊሆን ይችል ነበር?

   ______________________________

   ______________________________

2. ማንም ሰው የአባትን ፀፀት ከማማባስ በስተቀር ሊያመጣው የሚችለው ምንም ነገር የለም። የሚገርመው ነገር ዔሳው ብኩርናውን ከአቃለለው በኂላ በረከትን መፈለጉ ነው። በረከት ለእርሱ ምን ማለት ነው? ህይወትን ያለበረከት መኖር ምን ሊመስል ይችላል?

   ______________________________

   ______________________________

3. በክርስቶስ ኢየሱስ የባረከን የሰማያዊው አባታችን ከእርሱ ጋር ህብረት እንዲኖረን የሰጠን በረከት እንዴት ታላቅ ነው። እናንተስ ይህንን በረከት እንዴት ትረዱታላችሁ?

   ______________________________

   ______________________________

4. ዔሳው ከአባቱ በረከትን ለመቀበል በጣም ተነሳስቶ ነበር። እኛስ ከሰማዊው አባታችን በረከትን ለመቀበል እንደዔሳው ምን ያህል የተነሳሳ ልብ አለን? የግል አስተያየትህን ፃፍ፤

   ______________________________

   ______________________________

5. እንዴት አድርጋችሁ ከእግዚአብሄር በረከትን ለመቀበል ያላችሁን መነሳሳት የምትገልፁት?

   ______________________________

   ______________________________

## ክፍል 3

## ማሰላሰል

እስካሁን በአጠናናቸው ክፍሎች ላይ በግል የያዛችሁን ማስታወሻ እያነበባችሁ አሰላስሉ፡፡ እናንተ የፃፋችኋቸው ቃላት  እናንተን ራሳችሁን ማየት የምትችሉበት፤ ንስሃ የምትገቡበት፤ እና የእግዚአብሄርን ታማኝነት እያሰባቸው በጌታ የምትደሰቱበት ይሁን፡፡

## የግል ትግበራ

ማታለል ሊያደረስ የሚችለው አደጋ በሁላችንም ዙሪያ አለ፡፡ ቤተሰቦች በሰላም እጦት እየተበጠበጡ ነው፡፡ የተለያዩ ድርጅቶች በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ነው ያሉት፡፡ የተለያዩ አገራት የፖለቲካ መሪዎች ሲሰደዱና ክብራቸው ሲለያቸውና ሲናቁ ይታያል፡፡

1. በመታለላችሁ ወይንም በማታለላችሁ ሊከሰት የሚችለው አደጋ ምን ነበር?

   ________________________________________

2. ማታለሉስ ምን ነበር?

   ________________________________________

3. በማታለሉ ምክንያት የተበላሸ ግንኙነት አለ?

   ________________________________________

   ________________________________________

4. ምን አይነት የበደለኝነት ስሜትን መቀበል አለብን?  ምንአይነት ይቅርታስ መታወጅ አለበት?

   ________________________________________

   ________________________________________

   ________________________________________

እግዚአብሔር ጥፋታችንን እየተናዘዝን ወደ እርሱ እንድንመጣ ያበረታታናል፡፡ እውነት የህይወታችን አካል እንዲሆን ይፈልጋል፡፡  ይህ እውነት ደግሞ ኃጢአትን መናዘዝና የእርሱን ፍቅርና ምህረት መቀበልን የሚያጠቃልል ነው፡፡

## ፀሎት

ጌታ ሆይ በልቤ ውስጥ ማታለል አለ፤ ከዚህም የተነሳ ሰላም የለኝም፡፡ ከራሴ ውስጥ በሚመጣ ማታለል ተታልያለሁ፡፡ አንተ ግን እውነት ነህ፡፡ ቃልህ እውነት ነው፡፡ ኃጢአቴን ብናዘዝ ይቅር እንደምትለኝ  እና እንደምትቀበለኝ ገልፀህልኛ፡፡ ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስ ለልቤ ፈውስ እንደ ሆነ አምኜ ወደ አንተ መጥቻለሁ፡፡

## ክፍል 4

## መግቢያ

ያይቆብ ለእርሱ ያልተገባውን በረከት ወንድሙንና አባቱን በማታለል ተቀብሏል። ዔሳው ለእርሱ የተገባው በረከት ለወንድሙ እንደተሰጠ በአወቀ ጊዜ በጣም ተጎዳ፤ አባቱም እንዲባርከው ተማፀነ። ነገር ግን የሚሰጠው በረከት አልነበረም። ይስሐቅ ያይቆብን በወንድሙ ላይ ጌታ እንዲሆን ባርኮታል። በረከቱም በምድራዊ ፍሬ መባረክን ያጠቃልላል። አሁን ታሪኩ ይቀጥላል፤ ዔሳው ከአባቱ በረከትን ባለማግኘቱ ምክንያት አዝኗል።

**የቤት ስራ**

**ከዘፍጥረት** 27:41 እስከ ዘፍጥረት 28:9ድረስ ያለው ያንብቡ።

## ትምህርት

በክፍል 1 ነቢዩ ኤርሚያስ "የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው ማንስ ያውቀዋል?" ያለውን አይተነዋል። የማታለልን ሃይል በኤደን ገነት ውስጥ እንዴት እባቡ ሄዋንን በቀላሉ እንዳሳታ አይተናል። ማታለል የሰውን ልብ ኃጢአተኛነት የሚገልጥ ነው። ማታለል እንዴት የእግዚአብሄር አምሳያ በእኛ ውስጥ በኃጢአት ምክንያት እንደተበላሸ የሚያሳይ ነው። ከዚህም የተነሳ የተፈጠርንበትን ዓላማ ያም የእርሱን ክብር ማንፀባረቅ አልቻልንም።

## መልመጃ

በዘፍጥረት 27፡ 41 ላይ ያለውን ታሪክ ቀጥሉ፤

1. በቁጥር 41 መሠረት በዔሳው ሃሳብ ውስጥ የነበረው ምንድነው?

   ______________________________

2. ዔሳው ቂም እንዲይዝ ያደረገው ነገር ምንድነው (ቁጥር 41)?

   ______________________________

3. ምን ሊሰራ ነው ያሰበው (ቁጥር 41)?

________________________________________________

ይህ እቅዱ ሌሎች ሁለት ወንድማማቾችን እንድናስታውስ ያደርገናል።

________________፤ የሚባለው ________________ የሚባለው ወንድሙን ለመግደል ወሰነ (ዘፍጥረት 4:8).

4. ቂም ክፉን ይወልዳል። በኃጢአትና በክፉ ምኞት የተሞላ ቂም ወደ ነፍስ ግድያ ያመራል። ሐዋሪያው ጳውሎስ በኤፌሶን 4:26 የሚናገረን ምንድነው?

________________________________________________

________________________________________________

ለምን? እንቅልፍ ክፉው ወደሰው መግቢያ እንዲያገኝ ያደርጋል (ኤፌሶን4:27) እንዲሁም በአምዕሮአችን ውስጥ ክፉ ሃሳብ እንዲራባ ያደርጋል።

5. ርብቃ ዔሳው ሊያደረገው ያለውን ከሰማች በኋላ ለያይቆብ ነገረችው። ለያይቆብ የነገረችው ነገር ምንድነው ቁጥር 42?

________________________________________________

ዔሳው የአወጣውን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የአባቱን መሞት ይጠባባቅ ነበር።

6. ለሶስተኛ ጊዜ በምዕራፍ 27 ርብቃ ለያይቆብ የነገረችው ምንድነው (ቁጥር 43)፤

________________________________________________

ሌሎች ሁለት ተመሳሳይ የሆኑትን ከምዕራፍ 27 ፈልጉ እና ፃፉት፤

ሀ. ________________________________________

ለ. ________________________________________

7. የርብቃ መመሪያዎች "ቃሌን ታዘዝ" ፤ "የምለውን አድርግ" የሚል ነው። እነዚህ ነገሮች ስለእርሷ ባህሪይ ምንን ያስረዳናል?

________________________________________________

ከያይቆብ ጋር ያላት ግንኙነትስ?

________________________________________________

8. እንደ ቁጥር 43-45 የርብቃ እቅድ ምንድነው?

________________________________________________

9. ያይቆብ ፈጥኖ ስለሄደበት ምክንያት ለይስሐቅ ርብቃ የሰጠችው ምክንያት ምድነው (ቁጥር 46)? ዘፍጥረት 26:34-35 የተወሰነ ፍንጭ ይሰጠናል

____________________________________________________________

____________________________________________________________

10. በዘፍጥረት 28:1-2 ውስጥ ያይቆብ ከአባቷ ቤት ሚስት እንዲያገባ ርብቃ ያቀረበችው ሃሳብ ያይቆብ ተቀብሎታል፡፡ አባቱ አብረሃም ለእርሱ ሚስት ከካራን ምድር እንዲያመጣለት እንደላከ አስታውሱ፡፡ ይስሐቅ ለልጁ ያይቆብ የሰጠው መመሪያ ምንድነው?

____________________________________________________________

11. ያይቆብ ከመሄዱ በፊት ይስሐቅ ምን ብሎ ነው የባረከው (ዘፍጥረት 28:3-4)?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

12. እነዚህ ቃላት ለአያቱ አብረሃም እና ለአባቱ ለይስሐቅ እግዚአብሄር ከተናገራቸው ጋር ምን ግንኙነት አላቸው?

____________________________________________________________

13. በዘፍጥረት 28:5 ውስጥ ያይቆብ ____________________ወደሚባለው አጎቱ ____________________ ወንድም ወደሆነው ሄደ፡፡ የእነርሱ አባት ___________________________ ነው፡፡

ይህ የዘር ሐረግ እየሱስ በስጋ የሚወለደበት ስለሆነ ታሪኩ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ እግዚአብሄር ለአብረሃም ያደረገው ቃልኪዳን ለአብረሃምና ለዘሩ ነው፡፡

## ክፍል 5

ጥልቅ ጥናት

1. ያይቆብ ወደ አጎቱ ላባ ቤት ከሄደ በኋላ ዔሳው ምን ለማድረግ ያስብ ነበር (ቁጥር6-9)?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

2. የዔሳው ተግባር ምንን ያስተምረናል? በእርሱ ላይ የሆነው ምንድነው?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

3. እስማኤል ማን እንደሆነ አስታውሱ፡፡ እስማኤል የዔሳው አጎቱ ነው፡፡ የይስሐቅ የአባቱ የአብረሃም ልጅ ነው፡፡ ዔሳው ወደ አጎቱ እስማኤል ቤት ሚስት ፍለጋ መሄዱ ይስሐቅን የሚያስደስተው ይመስላችኋል? ያይቆብ ግን የሄደው ወደ እናቱ ወንድም ቤት ነው፡፡

ለዔሳው ወደ አጎቱ እስማኤል ቤት ሚስት ፍለጋ መሄዱ ችግሩ ምንድነው? የእግዚአብሄር መልአክ እስማኤልን አስመልክቶ ለአጋር የተናገራትን አስታውሱ ዘፍጥረት16:11-12.

______________________________________________________________

______________________________________________________________

ዘፍጥረት 25:18

______________________________________________________________

## ማሰላሰል

ከያይቆብ ጋር ወደ ካራን ምድር ከመጓዛችን በፊት እስኪ ጊዜ ወስደን እስከ አሁን ያጠናነውን እንመልከት። ቤተሰቡ ተከፋፍሏል። ወንድማማቾቹ በጠላትነት ይፈላለጋሉ። ወላጆች በልጆች መካከል ልዩነት በማድረግ ወገንተኛ ሆነዋል። አባት ከአባቱ አብረሃም የተላለፈለት በረከት አለው። ገና በማህፀን ውስጥ እያሉ ጌታ ለርብቃ ሁለቱ መንትያዎች እንደሚለያዩ እና ታላቁ ለታናሹ እንደሚገዛ ተነግሯታል። በትክክል የሆነው ይኸው ነው።

ያይቆብ ብኩርናን እና የአባት በረከትን ተቀብሏል። እነዚህ ለዔሳው የተገቡ ነበር ነገር ግን እርሱ ስለአቃለላቸው እና አባቱ ስለተታለለ አሁን የያይቆብ ሆነዋል። ዛሬም ተመሳሳይ ታሪኮች አሉ። በሆነው ነገር ሁሉ ተጋጭተው የማይነጋገሩ እህትማማቾች እና ወንድማማቾች አሉ። ጥላቻ ነግሷል፤ ቂምና ጥላቻ ነግሷል፤ ፍቅር ጠፍቷል።

የይስሐቅ ቤተሰብ የወደፊት እጣ ፈንታ አደጋ ላይ ወድቋል? የቃልኪዳኑ ጉዳይ ቀጣይነትስ ምን ይመስላል? ይስሐቅ የተስፋው ወራሽ ነው። እርሱ ሁለት ልጆች ብቻ ነበሩት ነገር ግን እነርሱ መስማማት አልቻሉም። አንደኛው ልጁ ወንድሙ እንዳይገድለው ፈርቶ ሸሸ፤ ታዲያ በዚህ ውስጥ እግዚአብሄር የት ነው ያለው? እግዚአብሄር ይህንን ቤተሰብ ተወውን? እርሱ ከአብረሃምና ከዘሩ ጋር ያደረገውን ቃልኪዳን ተወው? በቤተሰቡ ውስጥ የነበረው ማታለል የእግዚአብሄርን አጠቃላይ እቅድ የአዘበራረቀው ይመስላል። የእናንተ ሃሳብ በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ ምንድነው፤

______________________________________________________________

______________________________________________________________

የማሰላሰል ወይንም የምልከታ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ አላቸው ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ሊሆን የሚችለውን እንድናስብ ያግዙናል። የምልከታ ጥያቄዎች ከበድ ያሉ ጥያቄዎችን እድናነሳ ያደርጉናል። በዚህ ሁሉ ውጥንቅጥ ውስጥ እግዚአብሄር የት ነው ያለው? ምን

እያሰበ ነው? የሚያደርገው ነገር አለን? ተቆጥቶ ነበርን? እየሆነ ያለውን ማታለል እግዚአብሄር አፅድቆታልን? በተበላሸ ቤተሰባዊ ግኙነት ውስጥ እግዚአብሄር ፈቃዱን ይፈፅም ይሆንን? ስለእነዚህ ጉዳዮች ምን ታስባላችሁ፤

ከእነዚህ በተጨማሪ ከበድ ያለ ጥያቄ መጠየቅ የምትፈልጉትን ፃፉት

## ፀሎት

ጌታ ሆይ ስለይስሐቅና ቤተሰቡ እያጠናሁ በሄድኩኝ ቁጥር በዚያ ቤት ከሆነው ተግባር አኳያ እኔም የተግባሩ ተካፋይ እንደሆንኩኝ እየተሰማኝ ነው። እርስ በእርሳችን አንዳችን አንዳችንን በመበደላችን ምክንያት ሰላምን አጥተናል። ስለዚህ በደላችንን ይቅር በለን፤ የተበላሸውን ግንኙነታችንንም አድስልን።

# ክፍል አራት

# ከቤርሳቤህ ወደ ካራን

# ዘፍጥረት 28 እና 29

# አታላዩ ተታለለ

---

### የትምህርት አራት ቅኝት

**ቅኝት**

***መግቢያ***

ትምህርት 4፤ ዘፍጥረት 28 እና 29

- የያይቆብ ህልም
- ያይቆብ የቃልኪዳኑን ተስፋ ተቀበለ
- በካራን ምድር ዘመዶቹን አገኘ
- ያይቆብ ተታለለ
- ትግበራና ምልከታ

# *መግቢያ*

*ያይቆብ በሁሉም ነገር አብራው የነበረችውን እናቱን ፤ በሃዘን ልቡ የተሰበረወውን አባቱን እና ሊገድለው የሚፈልገውን ወንድሙን ትቶ ነፍሱን ለማዳን ሲል ሸሸ። ወደ ካራን ምድር እየሸሸ እያለ በመንገዱ ላይ የገጠመው ነገር ህይወቱን ቀየረው። እንደዚህ ህይወቱን የቀየረው ነገር ምን ሊሆን ይችላል?*

*ያይቆብ ወደ ካራን ምድር ከደረሰ በኋላ የእናቱን ወንድም አጎቱን አገኘው። ከእነዚህ ዘመዶቹ ጋር የሚኖረው ህይወቱ ምን ሊመስል ይችላል? ራሄልን ከወደዳት በኋላ በአባቷ የማታለል ተግባር የያይቆብ ህይወት የተወሳሰበ ሆነ። በአባቷ ታማኝነት የጎደላቸው ተግባራ ነገሮች ሌላ መልክ እየያዙ መጡ። እነዚህ ልብን የሚያሳምሙ ተግባራት ምንድን ናቸው? ህመሙንስ የተሸከመው ማነው?*

*ይህ ክፍል ህይወታችንን በስርዓት እንድመራው ይረዳናል። ጌታ እግዚአብሄር በቃሉ እና ከህዝቡ ጋር የሚያደርውን ግንኙነት ስታጠኑ ህይወታችሁን ከዚያ አንፃር መምራት እንድትችሉ ነገሮችን በጥንቃቄ አጥኑአቸው።*

## <u>ክፍል 1</u>

# ትምህርት

*ፓትሪያሪክ የሚለውን ቃል እንደምታውቁት ተስፋ አደርጋለሁ። አብረሃም ፤ ይስሐቅ እና ያይቆብ በቢሉይ ኪዳን ውስጥ የታወቁ ፓትሪያርኮች ናቸው። ፓትሪያሪክ የሚለው ቃል የመጣው ፓትሪ ከሚለው የላቲን ቃል ሲሆን ትርጉሙ አባት ማለት ነው። እነዚህ ሶስት ሰዎች የአይሁድ ህዝብ እና የእስራኤል አባቶች ናቸው። በዘፍጥረት* 28:10-22 *ላይ እግዚአብሄር ያይቆብን የቃልኪዳኑ ልጅ እንዲሆን እንደመረጠው ተመልክተናል።*

# የቤት ስራ፤

*ዘፍጥረት* 28:10-22 *ያንበብቡ። ያይቆብ ቤርሳቤህን ትቶ ወደ ካራን ምድር ወደ አጎቱ ወደ ላባ ዘንድ በመሸሽ ላይ ነው (ዘፍጥረት* 28:10) ።

## መልመጃ

1. ያይቆብ በመንገድ ላይ ም እያደረገ ነው (ቁጥር 11)?

______________________________

______________________________

2. በቁጥር 12 ላይ ያየውን ህልም ግለፅ/ጪ

______________________________

ሀ. እንደ ቁጥር 13 በመሰላሉ አናት ላይ የነበረው ማነው?

______________________________

ለ. እኔ ማነኝ አለ?

______________________________

ሐ. ምንን እሰጣለሁ አለ?

______________________________

መ. በቁጥር 14ሀ ለያይቆብ ዘር ምን ሊያደርግ ቃል ገባ?

______________________________

______________________________

ሠ. በያይቆብና በዙ የሚባረከው ማንነው (ቁጥር 14ለ)?

______________________________

______________________________

3. በቁጥር 15 እርሱ ምን ተስፋ ሰጠ?

ሀ. እኔ ______________________________

ለ. በምትሄድባትም ______________________________

ሐ. ወደዚህች ______________________________

መ. የነገርኩህን ______________________________

4. ስለሚወርሰው ምድር እና ስለዘሩም ቃል ተገብቶለታል። ለአብረሃም እና ለይስሐቅ የተገባው ቃልኪዳን ለእርሱም ተገብቶለታል። የእግዚአብሄርን መገኘት አውቆታል። ለዚህ ደግሞ የያይቆብ ምላሽ ምን ነበር ቁጥር 17?

______________________________

5. ምን አለ?

______________________________

6. ይህንን ህልም ያየው እኩለ ሌሊት ነበር፤ ሲነጋ ምን አለ ቁጥር 18?

___

___

7. ያንን ስፍራ ምን ብሎ ሰየመው? ____________________:: ቤቴል የሚለው ቃል የሁለት ቃላት ጥምር ነው። ቤት ማለት እንደአማርኛው ቃል ቤት ማለት ሲሆን፤ ኤል ማለት ደግሞ አምላክ ወይንም እግዚአብሄር ማለት ነው።

8. በቁጥር 20-22 ላይ ያይቆብ ቃለ መሃላ ገባ። ቃለ መሃላው "ከእኔ ጋር ቢሆን ____________________________ይሆንልኛል" የሚል ቃላትን ያጠቃለለ ነው።

   ሀ. "ከእኔ ጋር ቢሆን" የሚለው ምንን ያመለክታል?

   ___

   ___

   ለ. "ይሆንልኛል" የሚለውስ ምንን ያመለክታል?

   ___

   ___

   ያይቆብ እግዚአብሄር ከእኔ ጋር ቢሆን ሲል 1) ከእርሱ ጋር ቢሆንና ቢጠብቀው 2)ምግብና እና ልብስ ቢሰጠው፤ እንዲሁም 3) ወደ አባቱ ቤት በሰላ ቢመልሰው፤ ከዚያ 1) ጌታ አምላኩ ይሆናል 2) ድንጋዩ ወይንም መሰዊያው የእግዚአብሄር ቤት ይሆናል፤ 3) እግዚአብሄር ከሚሰጠው ሁሉ አስራቱን መልሶ ለእግዚአብሄር ይሰጠዋል።

9. ዘፍጥረት 28:22 የመጀመዊያው ስለአስራት የተጠቀሰው በዚ ስፍራ ላይ ነው። የአስራት አሰራር የሚያስታውሰውን ሁሉንም ነገር የተቀበልነው ከእግዚአብሄር መሆኑን ነው። እርሱ የሚያስፈልገንን ሁሉ ያደርግልናል።

# ክፍል 2

# ማሰላሰል

ያይቆብ ነፍሱን ለማዳን ሲል ሸሽቶ ወደ አጎቱ ወደ ላባ ቤት እየሄደ ነው። በጎዞው ላይ እያለ ድንጋይን ተተንተርሶ በተኛበት አንድ ነገር ሆነ። ህልምን አለመ፤ የአለመው ህልም ከዚህ በፊት የሚያውቀውን ነገር አይደለም። ወይንም ይህ ተራ ህልም አይደለም። ህልሙም እግዚአብሄር ወደ እርሱ መጥቶ ለአብረሃም እና ለይስሐቅ የገባውን ቃል ኪዳን ለእርሱም ቃል የገበባት ነበር። ምድሪቱ የእርሱ እንደሚሆን እና ዘሩ ደምድር ላይ እንደምድር አሸዋ እንደሚበዛ

የሚያመለክት ነው። ከሁለም በላይ የምድር ነገዶች በእርሱ እና በዘሩ እንደሚባረኩ ቃል ተገብቶለታል። ያይቆብም በዚያ ስፍራ የጌታን መገኘት ከተገነዘበ በኋላ ለእግዚአብሄር መሰዊያን ሰራ።

ይህ ለያይቆብ አዲስ ጅማሬ ነው። ህይወቱ ሌላ አቅጣጫን የያዘበትም ነው። ያይቆብ ከዚህ በፊት የአባቱን አምላክ ተቀብሎት ይሆንን? እግዚአብሄር ለእርሱ ምን ማለት ነበር? ምንም? በዚያ ስፍራ የእግዚአብሄር መገኘት በግልፅ አለ። ያይቆብም ፈርቶ ነበር። ያንን ስፍራ ተራ ቦታ እንዳልሆነና የእግዚአብሄር መገኛ የሰማይ ደጅ እንደሆነ ተገነዘበ። በዚያ ሌሊት እና በሚቀጥለው ማለዳ ለያይቆብ ህይወት የተለየች እንደምትሆን ማሰብ ይችላል። እርሱም እግዚአብሄርን ሊፈትነው ተዘጋጅቷል። እኔ ልገደል ስልሆነ ጠብቀኝ፤ ምንም ነገር ስለሌኝ ምግብና ልብስ ስጠኝ። እኔ ከቤቴ፤ ከቤተሰቦቼ፤ከለመድኩትና ከምወደው ነገር ሁሉ ተለይቼ እየሸሸሁ ነው። ስለዚህ በሰላ ወደ ቤቴ መልሰኝ። ምን አይነት ጥያቄዎች ናቸው። እንደያይቆብ የልቤን ሁሉ ዘርዝሬ ለጌታ ነግሬው ይሆንን?

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

እርሱ እንደ አባትነቱ ለእኔ ለልጁ እንደሚንከባከብ ለማወቅ ምን ማድረግ አለብኝ?

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

ያይቆብ ጌታ አምላኩ እንደሚሆንና ከዚያም እግዚአብሄር ከሚሰጠው ሁሉ አስራቱን መልሶ ለእግኢአብሄር እንደሚሰጠው ቃል ገባ። የያይቆብ አምላክ የአንተ/ቺም አምላክ ነውን? የልብህን/ሽን ፍላጎት እንደሚያውቅና እንደሚያሟላ ታውቃለህ/ታውቂያለሽ? ያይቆብ ከእግዚአብሄር ጋር ያለውን ህብረት የገለጠበት መንገድ አስራትን በመስጠት ነበር። አንተ/ቺ ከጌታ ጋር ያለህን/ሽን ህብረት በምን ትገልፃለህ/ሽ?

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

## ፀሎት

እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ስለያይቆብ እና ስለዔሳው ብዙ ባጠናው ቁጥር ስለ ራሴ ብዙ እያወኩኝ ነው ። ስለዚህ አመሰግንሃለው። ስለ እራሴ ካወኳቸው ነገሮች እኔ ለጥቅሜ ስል ብዙ አጭበርብሪያለሁ። ሰዎችን ገፍቻለው እና ይቅር በለኝ። በእኔ አጭበርባሪነት የተበላሸውን ግንኙነት ሁሉ እንድትፈውስ እለምንሃለው።

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

## ክፍል 4

# ትምህርት

በያይቆብ ህይወት ውስጥ እነዚያ ተደራራቢ ነገሮች ካለፉ በኂላ አሁን መጠለያ የሚሆነውን ቤት አግኝቷል፡፡ የአጎቱ ቤተሰቦች ምንም ከዚህ በፊት አግኝተውት ባያውቁም እንኳን አሁን እንደ ቤተሰባቸው አባል አደርገው ተቀብለውታል፡፡ ያይቆብ በላባ ቤት ውስጥ መጠጊያ አገኘ፡፡ አሁን ያይቆብ በአዲሱ ቤተሰብ ውስጥ ምን አይነት ባህሪይ እንደሚያሳይ እና ምን እንደሚገጥመው በዚህ ትምህርት ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

# የቤት ስራ

ዘፍጥረት 29:14-30. አንብቡት፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ያልገባችሁ ቃል ካለ አስምሩበት፡፡ ግን በክፍሉ ውስጥ ለላባ እና ለርብቃ ቤተሰብ አንድ አስፈሪ ነገር ተከስቷል፤ነገሩ ምድን ነው?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

መልመጃ

1. ላባ በቁጥር 15 ላይ ያይቆብን የጠየቀው ጥያቄ ምንድን ነበር? ________________

   ______________________________________________________________________

2. በቁጥር 16 እና 17 መሰረት ላባ ሁለት ልጆች እንዳሉት እንረዳለን፡፡ ታላቂቱ ልጁ ______________ ትባላለች፡፡፡ ታናሽተዋ ደግሞ __________________________ናት፡፡

   ሀ. ልያ በክፍሉ ውስጥ እንዴት ነበር የተገለጸችው?

   ______________________________________________________________________

   ለ. ራሄልስ በክፍሉ ውስጥ እንዴት ነበር የተገለጸችው?

   ______________________________________________________________________

3. በቁጥር 18 መሰረት ያይቆብ ራሄልን ይወዳት ነበር፡፡ እናም ላባ አንድ ያቀረበለት ድርድር ምንድን ነበር?

____________________________________________________________

____________________________________________________________፡፡

4. ራሄል ሚስቱ እንደምትሆን ባወቀ ጊዜ ያይቆብ ለላባ ሊሰጠው የተስማማውን አገልግሎት እንዴት ትመለከተዋለህ/ ትመለከችዋለሽ (ቁጥር 20)?

____________________________________________________________

5. እነዚያ ________ አመታት ከተፈጸሙ በኋላ የአገልግሎቱን ዋጋ ራሄልን ከእርሱ ጋር እድትሆን ያይቆብ ላባን ጠየቀው፡፡ ላባም በግብዣ እና በድግስ ልጁን ለመስጠት ተስማማ፡፡ በቁጥር 22 መሰረት ምን ነበር ላባ ያደረገው?

____________________________________________________________

6. ግን ታሪኩ በጣም እየተወሳሰበ ነበር የሄደው በቁጥር 23 መሰረት ላባ ምነድን አደረገ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

አሁን የያይቆብ ሚስት የሆነችው ሊያ ናት፡፡ ከዚያም ለሊያ አንድ አገልጋይ ሰጣት የዚህችም አገልጋይ ስም ________________________ ነበር፡፡

7. በነጋም ጊዜ እውነቱ ተገለጠ፡፡ ከያይቆብ አጠገብ የተኛችው ሊያ መሆንዋን ያይቆብ ተረዳ፡፡ ያይቆብም በቁጥር 25 መሰረት ወደ ላባ ሄዶ ምንድን ነበር ያለው?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ያይቆብም እኔ ያገለገልኩ ለራሄል ኤደለምን ብሎ ጠየቀው፡፡ ከዚያም እውንቱን ገልጦ ተናገረው፡፡

____________________________________________________________

8. ያይቆብ ን ከአጭበረበረው በኋላ ላባ በቁጥር 26 ላይ ምንድን ነበር ያለው?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

በባህላቸው መሰረት ታላቂቱ ልጅ ሳታገባ ታናሺቱ ማግባት አትችልም ነበር፡፡ ከዚያም በኋላ ለያይቆብ ራሄልን ሊድርለት እና ስለራሄልም ያይቆብ ተጨማሪ ሰባት አመታትን ሊያገለግለው ተስማሙ፡፡ ቁጥር 28 እንዲህ ይላል

_____________________________________________________________::

በዚህም መሰረት ላባ ለያይቆብ ራሄልን ሚስት እንድትሆነው ______________ሰጠው (ቁጥር 29)።

9. ቁጥር 30 ያይቆብ ከሁለቱ ሚስቶቹ ጋር ስለነበው ግንኙነት ይነግረናል። እርሱ ያደገበት ቤት ወላጆች ልጆችን እያበላለጡ የሚወድዱበት ቤት ነው። አሁን ደግሞ እርሱ በራሱ ቤት አንዷን ሚሲቱን ከሌላዋ አብልጦ እየወደደ ነው። ከመጀመሪው ስምምነታቸው በተጨማሪ ለላባ ተጨማሪ ___________________ አመታትን አገለገለ።

# ማሰላሰል

1. በዚህ ክፍል ውስጥ አንድ በደንብ ልናስበው የሚገባው ጉዳይ የሊያ ጉዳይ ነው። ምንም እንኳን አሁን ለያቆብ ሚስት ሆና ብትሰጥም እና ከእርሱ ጋር ትዳር ብትጀምርም አንድ መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን ነገር ያይቆብ እርሷን እንደማይወዳት ነው። እናም አንድ ጥያቄ እራሳችንን እንጠይቅ። እንዲያው የማይወዳትን ባል አግብታ መኖር ለእርሷ ምን አይነት ስሜት ፈጥሮባት ይሆን? እንደ እህቷ ቆንጆ እንዳልሆነች እናውቃለን። መጽሐፍ ቅዱስ ሲነግረን ቆንጆ አይደለችም ይለናል። እናም ደግሞ እድሜዋ ሄዷል ከዚህ በተጨማሪ ፈላጊ አግኝታ አላገባችም። እህቷ ራሄልን ነበር ያይቆብ ሊያገባ የፈለገው። ሊያ ባህሉን በደንብ አድርጋ ነው የምታውቀው። ከእነዚያ ሰባት የአገልግሎት አመታት በኋላ አባትዋ ላባ ራሄል ናት ብሎ እርሷን ለያይቆብ ሊሰጥ እንዳሰበ ታውቅ ነበርን? ከዚያም ያይቆብን አግብታው ስታበቃ በነጋታው የእርሱ ሚስት ልትሆን እንደማይገባ አስቦ ሲቆጣ ስታይ ምን አይነት ስሜት ይሰማት ይሆን?
2. እስኪ እራሳችሁን ሊያን ቃለመጠይቅ ለማድረግ እንደተላከ ጋዜጠኛ አድርጋችሁ አስቡ። እርሷን ስታገኙ መጀመሪያ መጠየቅ የምትፈልጉት ጥያቄ ምንድን ነው? ለእናንተም ሆነ ለሚያዳምጯችሁ ሰው በጣም አስገራሚ እና አሳሳቢ ጥያቄ ይሆናል ብላችሁ የምትገምቱት ምንድን ነው? ሊያ እራስዋ በዚህ የማጭበርበር ድራማ ውስጥ ያላት ሚና ምንድን ነው? ሳታውቀው እርስዋም በአባትዋ ተንኮል የተያዘች ሴት ትሆን እንዴ? እርስዋ ቆንጅና እና መልክ ስለሌላት የሚሰማት ስሜት ምን አይነት ይሆን? እናንተ ሁሌ ጊዜ ከእናንተ ይሻላል ተብሎ ከሚገመት ታላቅ ወይንም ታናሽ እህት ጋር ብትነጻጸሩ ምን ይሰማችሁ

ይሆን? እስኪ ጊዜ ወስዳችሁ ለሊያ ማቅረብ የምትፈልጉትን ተጨማሪ ጥያቄዎችን አስፍሩት:

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

# ክፍል አምስት

# ትግበራ

1. ምን አልባት እናንተ የሰውን ተቀባይነት ለማግኘት ተወዳድራችሁ አታውቁም ይሆናል፤ ምን አልባትም በሰው ዘንድ ለመፈቀር ብዙ ታግላችሁ አታውቁም ይሆናል። ግን ታግላችሁ የምታውቁ ከሆነ የእናንተ ተቀናቃኝ የነበረው ማን ነው? ያ የእናንተ ተፎካካሪ ከእናንተ ተሽሎ የተገኘበት መንገድ ምን ይሆን?

   ____________________________________________________________

   ____________________________________________________________

2. እናንተ ሁል ጊዜ እንዲኖራችሁ የምትፈልጉት እና ቢኖራችሁ ከሰው እኩል ያደርገኛል ብላችሁ የምታስቡት ነገር ምንድን ነው?

   ____________________________________________________________

3. ሰዎች እናንተን እንዴት ነው የሚመለከቷችሁ? የእናንተ ልምምድስ ምን ይመስላል?

   ____________________________________________________________

   ____________________________________________________________

4. እነርሱ እናንተን በዚህ መልኩ እንዲመለከቷችሁ እንዴት ፈቀዳችሁ?

   ____________________________________________________________

# ፀሎት

እግዚአብሔር ሆይ እራሴን ከሌሎች ጋር ሳስተያይ በብዙ ያነስኩ መስሎ ይሰማኛል። ይህ ብቻ አይደለም ብዙዎች ከእኔ የሚሻሉበት ነገር እንዳለ አስባለው። እናም ብዙጊዜ

እራሴንም መውደድ ያቅተኛል። ሌሎች ከእኔ የተሸለ ችሎታ፣ ገንዘብ፣ መልክ፣ ቁመና፣ እና ብዙ መልካም ነገር እንዳላቸው ስለማስብ እራሴን እጠላዋለው። ዛሬ ግን እራሴን መቀበል እንድችል እና ልክ አንተ እድፈጠርከኝ ያለኝን መልካም ነገሮች መገንዘብ እንድችል እና እኔን በእኔነቴ ውድ አድርገህ ስለፈጠርከኝ አመሰግንህ ዘንድ እርዳኝ።

---

---

## ማሰላሰል

አንድ ከያይቆብ ህይወት ጋር የተያያዘ እና ትኩረት የሚፈልግ ጉዳይ አለ። አሁን ያይቆብ እራሱ እየተጭበረበረ ነው ያለው። እርሱ እና ላባ ስምምነት ነበራቸው። እርሱ ላባን ለሰባት አመት ሊገለግለው እና የሚወዳትን ራሄል ደግሞ ላባ ሊሰጠው ነበር የተዋዋሉት፤ በዚህ መሰረትም ደግሞ ለባን ያይቆብ ሰባት አመት ሙሉ አገልግሎታል። እናም ሰባቱ  አመታት በተፈጸሙ ጊዜ የሚወዳትን እና ለአመታት የጠበቃትን ራሄልን ለመቀበል ነበር የያይቆብ ዝግጅት፡፤ እናም እርሱ ወደ ድንካኑ ወስዶ አብሯት ሊኖር ፈለገ። ነገር ግን ደግሞ ምሽት ስለነበር ላባ ለማጭበርበር ተመቸው። ከዚያም እህቷን ሰጠው። ያይቆብ ሊያ እንደሆነች ባወቀ ጊዜ ሊሰማው የሚችለውን ስሜት እስኪ ገምቱት።

አንድ ሰው ተጭበርብሮ መጭበርበሩን ባወቀ ገዜ ምን ይሰማዋል? ወደ ኋላ  መለስ ብለን በዘፍጥረት ሶስት ላይ አዳም እና ሄዋንን ይህንን ጥያቄ መጠየቅ እንችላለን። ሁለቱም አይናቸው ተከፍቶ ነበር። እናም በስተመጨረሻ እንደተታለሉ ገባቸው። እኛም በህይወታችን ስንጭበረበር ከዚያም የተሰራብንን ሸር ስናውቅ ምንድን ነው የሚሰማን?

## ግላዊ ትግበራ

1. እንደው በሕይወታችሁ ያመናችሁት ሰው ከድቶአችሁ ያውቃል? ያ የከዳችሁ ሰው ማን ነበር ነገሩስ ምንድነው?

---

---

2. እናንተስ ለዚያ የማጭበርበር ተግባር የነበራችሁ ምላሽ ምንድን ነበር?

________________________________________________________________

________________________________________________________________

## ፀሎት

እግዚአብሔር አምላክ ሆይ አንተ የእውነት አምላክ ነህ። ሀሰትም በአንተ ዘንድ የለም። እናም አንተ ማታለልን ትጠላለህ፣ እኔ ግን አንዳንድ ጊዜ በጥቅም በመታለል እና የምፈልገውን አገኛለው በማለት ብዙ ጊዜ ሰዎችን አታልዬ አውቃለሁ እና ይቅር በለኝ።

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________።

# ክፍል አምስት

# ራሄልን ከሊያ በላይ ይወዳት ነበር

# ዘፍጥረት 29 እና 30 — የያይቆብ ወንድ ልጅ መወለድ

---

አጠቃላይ ምልከታ

መግቢያ

ትምህርት 5: ዘፍጥረት 29 እና 30

- ሊያ እና ያይቆብ ልጆችን ወለዱ
- የራሄል ቅናት እና የሊያ ብቸኝነት
- ራሄል መካን ሆና ቀረች
- ራሄል ወንድ ልጅ ወለደች
- ቅናት እና ፍርሃት

# የቤት ስራ

ዘፍጥት 29:31 እስከ 30:24. ያለውን ክፍል አንብቡት። እናም በዚህ ክፍል ውስት ለያይቆብ የተለዱለትን ልጆች ስም እያሰመራችሁበት ሄዱ።

## መልመጃ

ከዚህ በታች ያለውን ሰንጠረዥ

| የእናት ስም | የልጅ ስም | የስሙ ትርጉም |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

1. በቁጥር 31 ላይ እግዚአብሔር ሊያን በልጆች ባረካት። ግን በዚህ ክፍል ስለ ራሄል ምን እንረዳለን?

______________________________________________

______________________________________________

2. ሊያ በቁጥር 32 መሰረት ስለራስዋ የነበራት አመለካከት ምን ይመስላል?

______________________________________________

ምኞትዋስ ምን አይነት ነው? ______________________________

3. በቁጥር 33 ላይ ሊያ እንደገና ፀንሳ እናገኛታለን፡፡ የወንድ ልጇን ስም ማን አለችው? ስሙስ ትርጉም ምንድን ነው፡፡ ስለ ልጇስ ምን አመነች?

______________________________________________

______________________________________________

እርሷ አሁን እግዚአብሔር እየባረካት እንዳለ እርግጠኛ ሆና ነበር፡፡ ለምን?

______________________________________________

የልቧ የመጨረሻ ምኞት ምንድን ነበር?

______________________________________________

______________________________________________

# ክፍል 2

## ቀጣይ መልመጃ

1. በቁጥ 34 መሰረት ሊያ ሶስተኛ ልጅ ወለደች፡፡ የልጇን ስም ማን አለችው? ትርጉሙስ ምንድን ማለት ነው?   አሁን ሊያ ምን ይሆናል ብላ አመነች?

______________________________________________

ሀ. ሊያ ከባልዋ ጋር አንድ ለመሆን በጣም ፈልጋለች፡፡ ግን ሚስት ሳይሆን ለባልዋ አገልጋይ እንደሆነች እንዲሰማት የሚያደርግ ነገር ምንድን እንመለከታለን?

______________________________________________

______________________________________________

ለ. ስለ ሊያ ህመም ይህ ቁጥር ምን የተለየ ነገር ይነግረናል?

______________________________________________

______________________________________________

2. በቁጥር 35 መሰረት ሊያ እንደገና ፀነሰች እና ወንድ ልጅ ወለደች። ስሙንም ማን አለችው ትርጉሙስ ምንድን ነው? ሊያ አሁን በህይወቷ ወሳኝ ወደ ሚባል ምዕራፍ ተሸጋግራለች። አሁን የሊያ ራሄልን እያየች መሰቃየት አቁማለች። ይህ በህይወቷ የጎደለው ነገር ________________________________ ነበር።
ግን የዚህን የአራተኛ ልጇን መወለድ አጋጣሚ እንደ በረከት አየችው። አንድ መልካም የሆነ ________________________ ነገር ለመቀበል ተዘጋጅታ ነበር።

3. የቁጥር 35 መጨረሻ ምንድን ይነግረናል? ________________________________
____________________________________________________________

4. ይህ ሆኖ ሳለ ዘፍጥረት 30:1 ላይ በራሄል ሕይወት ውስጥ ምንድን እየሆነ ነው?
____________________________________________________________

ሀ. ራሄል በእህቷ ላይ ______________________ .

ለ. ቅናት የመገፋት ፍርሃት የሚፈጥረው ስሜት ነው። ይህ ትርጉም ከራሄል ህይወት ጋር እንዴት ይሄዳል?
____________________________________________________________
____________________________________________________________

ሐ. ከያይቆብ አሁን እርስዋ ምንድን ፈለገች?
____________________________________________________________

ሐ. አሁን በቁጣ መጣም እንደተሞላች ማየት ይቻላል ምክንያቱም
____________________________________________________________
____________________________________________________________

የሳራ ታሪክ በዘፍጥረት 16:2 ላይ እንደምንመለከተው ያይቆብ ራሄል ልጅን እንዳትወልድ እግዚአብሔር ማህፀንዋን እንድዘጋው ነበር ያመነው። (ዘፍጥረት 30:2).

መ. በቁጥር 3 ላይ ራሄል ለያይቆብ ምን አለችው?
____________________________________________________________

ራሄል አሁን ህይወታን በቅናት ፍርሃት ነው የምትመራው። አሁን ትልቁ ፍርሃትዋ የያይቆብ ፍቅር ከእርስዋ ተወስዶ አራት ልጅ ለወለደችለት ለእህትዋ ለሊያ ይሆናል የሚል ነው። የያይቆብን ፍቅር በራስዋ ዘንድ ለማቆየት በጣም ፈለጋለች።

1. በዘፍጥረት 30:4-6 ራሄል ለያቆብ ሚስት ትሆነው ዘንድ አገልጋይዋን አስገባችለት። እናም ያይቆብም አብሯት ተኛ። ከያቆብም አረገዘች። የተወለደውን ልጅ ማን ብላ ሰየመችው? ትርጉሙስ ምንድን ነው?

    ሀ. ስሙን ያወጣው ማን ነው? ___________________________

    ለ. በወቅቱ በመካን ሴቶች ላይ የነበረውን መገለል አስቡ እና ራሄል ይህንን ስም ለምን እንደመረጠች ገምቱ?

    __________________________________________ አሁን የተሻለ ስሜት ተሰምቷታል። እግዚአብሔር ወንድ ልጅን ሰጣት። አሁን ህብረተሰቡ እንደ ክፉ እና እንደተቀጣች ሴት አይመለከታትም። ከነቀፋ ነጻ ሆናለች።

# ክፍል 3

# የቀጠለ መልመጃ

ዘፍጥት 30

2. ቁጥር 7 እና ስምንት ላይ እንደምንመለከተው የራሄል አገልጋይ የሆነችው ለያይቆብ አሁንም አረገዘች። የልጁ ስም ማን ተባለ? ትርጉሙስ ምንድን ነው? አሁንም ለልጁ ስም ያወጣችው ራሄል ነበረች። አሁን ያወጣችው ስም ስለእርስዋ ማንነት ምን ይነግረናል?

    __________________________________________________________________

    ________________________________________________________________።

    የራሄል ቅናት ከእህቷ ጋር ውድድር እንድትገጥም አድርጓታል። አሁን ከአገልጋይዋ ያይቆብ ሁለት ልጆችን እንዲወልድ ስላደረገችው እና ልጆቹ በእርስዋ ስለተጠሩ አሸናፊ የሆነች መስሎ እየተሰማት ነው።

3. ከቁጥር 9-11: ሊያ አሁን ልጅ መውለድ ስላቆመች አገልጋይዋን እርስዋም ለያይቆብ ሚስት እንድትሆነው ሰጠችው። እርስዋም ለያይቆብ ፀንሳ ወለደች። የተወለደው ልጅ ስሙ ማን ነው? ትርጉሙስ ምንድን ነው? ሊያ አሁንም ለያይቆብ ሌላ ልጅ እንዲወለድለት ማድረግ በመቻልዋ ደስተኛ ናት። ግን በዚህ ውስጥ የሊያ አመለካከት ምንድን ነበር?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

4. የሊያ አገልጋይ እንደገና ለያይቆብ ፀነሰችለት። አሁን የተወለደው ልጅ ስሙ ማን ነው? ትርጉሙስ ምንድን ነው? አሁን ሊያ ለማህበረሰቡ ያላት መልእክት ምንድን ነው?

 ____________________________________________________________

 ___________________________________________________________

 አሁን ሊያ ከባልዋ ያጣችውን ፍቅር ሁሉ ከእግዚአብሔር ያገኘችው ይመስላል። አሁን ሰዎች ሁሉ ከ ______________________ ይልቅ ለ ________________ ቦታ እንደሰጠች ይመለከታሉ። ቤተሰቡ ውስጥ የነበረው ቅሬታ እና ፍጅት ሁሉ አሁን አበቃ።

5. አሁን በሊያ እና በእህቷ እንዲሁም ደግሞ በአገልጋዮቹ መካከል ሁሉም ነገር ሰላም የሆነ ነው ሚመስለው። ቁጥር 14 እስከ 16 ያለውን ስንመለከት የሊያ ልጅ አንድ እጽዋት አግኝቶ ለእናቱ እንዳመጣ እናያለን። ልብ በሉ፡ ልጁ አግኝቶ ለእናቱ ያመጣላት እጽዋት በወቅቱ በሽታን ለማከም እና ለተለያዩ ጉዳዮች አገልግሎት የሚሰጥ ነበር። ራሄል አይታ ትሰጣት ዘንድ እህቷን ጠየቀቻት። ከዚያም በሁለቱ መካከል ያለው ጦርነት ብዙም እንዳልበረደ እንመለከታለን። ሊያ ምላሽዋ ምን ነበር?

 ____________________________________________________________

 __________________________________________________________ ።

6. ከዚያም በቁጥር 17-18 ላይ እንድምንመለከተው ሊያ እንደገና ፀነሰች። ከዚያም ወንድ ልጅ ወለደች። የተወለደውን ልጅ ማን ነበር ብላ የሰየመችው የስሙስ ትርጉም ምንድን ነው?

 ____________________________________________________________

 ____________________________________________________________

7. ሊያ ስድስተኛ ልጅ ደገመች። አሁን ከልጇ የተነሳ ምን ይሆልኛል ብላ ጠበቀች?

 ____________________________________________________________

 ____________________________________________________________

## ማሰላሰል

እስኪ አሁን ጊዜ ወስዳችሁ እራሳችሁን ጠይቁ፡፡ በእህትማማቾች መካከል ምንድን እየሆነ ነው ያለው? በዚህ ሁኔታ ውስጥ መኖርስ ምንድን ይመስላል?

______________________________________________________________________

_____________________________________________________________________፡፡

## ክፍል 4

### መልመጃ ፧ ዘፍጥረት 30

1. በቁጥር 21 ላይ እንደምንመለከተው ሊያ አንዲት ሴት ልጅ ለያይቆብ ወለደች፡፡ ስሟንም ዲና ብላ ሰየመቻት፡፡ ይህ ታሪክ የተነገረን በዘፍጥረት 34 ላይ ቀጥሎ የሚመጣውን ነገር መረዳት እንድንችል ነው፡፡ ይህንን ክፍል እኛ በጋራ ስለማናጠናው እባካችሁ በግል አንብቡት፡፡

2. ግን ራሄልስ ምንድን ሆነች? በቁጥር 22 ላይ እግዚአብሔር እንዳሰባት እንመለከታለን፡፡ እግዚአብሔር ፀሎትዋን ሰምቶ ማህንዋን ከፈተው፡፡ አሁን የወለደችውን ወንድ ልጅ ማን ብላ ሰየመችው? የስሙስ ትርጉም ምንድን ነው? አሁን በስተመጨረሻ የልጅ እናት ሆነች፡፡ እግዚአብሔር ነቀፌታዋን አስወገደው፡፡ አሁን የጠየቀችው ነገር ምንድን ነው?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

3. ምዕራፍ 29 እና 30 ላይ ለያቆብ ስለተወለዱት 11 ልጆች ታክ እናነባለን፡፡ ሆኖም በዚህ አላባቃም አሁን አንደገና አንድ ወንድ ልጅ ለያቆብ ተወለደለት፡፡ ስለዚህ ልጅ ታሪክ ለማጥናት ወደ ዘፍጥረት 35፡ 16-20 መሄድ አለብን፡፡.

ሀ. አሁን ያይቆብ ቤተሰቡን በሙሉ ወደ ቤቴል ይዞ መጣ፡፡ ቤቴል ያይቆብ ህልም ያየበት፣ ከእግዚአብሔር ጋር ቃልኪዳኑን ያደሰበት፣ አብርሃም እና ይስሐቀ የኖሩበት ስፍራ ነው፡፡ ከዚያም ከቤቴል ወደ ያቦቅ ወንዝ ተጓዙ፡፡ በቁጥር አስራ ስድስት መሰረት በዚያ ምን ተፈጠረ (ቁጥር 16)?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

ለ. በቁጥር 17 መሰረት አገልጋይዋ እንደገና ወንድ ልጅ እንደተጋለገለች ነገራት፡፡ አሁን ልጁን የሰየመው ያይቆብ ነበር፡፡ ያይቆብ ማን ብሎ ስም አወጣለት የስሙስ ትርጉም ምንድነው?

_______________________________________________

_____________________________________________

እግዚአብሔር የራሄልን ጥያቄ ሁሉ መለሰ፡፡ እናም እንደገና ሌላ ልጅ ወለደች፡፡ ግን በዚህ ወቅት በምጥ ላይ እያለች ራሄል ሞተች፡፡ ያይቆብ አሁን ቀኝ እጁ የተቆረጠ ያህል ተሰማው፡፡

ሀ. ራሄል አሁን ሞታለች፡፡ ያይቆብ ገና ወደ አባቱ ቤት ሳደርስ ነበር የተለየችው፡፡ በቁጥር 28 መሰረት ይስሐቅ አንድ መቶ ሰማንያ አመት ሙሉ ኖሮ እንደሞተ ተነግሮናል፡፡ ልጆቹ __________________ እና __________________ አብረው ቀበሩት (ቁጥር 29).

## ማሰላሰል

ይህንን የዘፍጥረት መጽሐፍን ስናጠና አሁንም እንደገና ወደ አዕምሮአችን የሚመጡ ብዙ ጥያቄዎችን አሉ፡፡ የግል አመለካከቶቻችን የቡድን ውይይታችን እንዲሁም ጥናቶቻችን የሚፈጥሩዋቸው ጥያቄዎች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ጥቂቶቹ

1. የያይቆብን ታሪክ ለማሰላሰል ጊዜ ውሰዱ፡፡ እያንዳንዱን በዚህ ታሪክ ውስጥ ያለውን ሰው ፊት ለፊት ብታገኙ ልትጠይቁ የምትወዱት ጥያቄ ምንድን ነው?

ሀ. ያይቆብን

_______________________________________________

_______________________________________________

ለ. ሊያን

_______________________________________________

_______________________________________________

ሐ. የሊያን አገልጋይን

_______________________________________________

_______________________________________________

መ. ራሄልን

______________________________________________________________

______________________________________________________________

ሠ. የራሄልን አገልጋይ

______________________________________________________________

______________________________________________________________

2. የግል የህይወት ልምምዶቻችን የሚፈጥሩብን ስሜት አለ፡፡ ይህንን ክፍል ስታነቡ የሚፈጠርባችሁን ስሜት መዝግቡ

______________________________________________________________

______________________________________________________________

# ክፍል 5

# ትምህርት

በዘፍጥረት 30:1 ራሄል በእህቷ ትቀና እንደነበር አውቀናል፡፡ ግን ደግሞ ከእህቷ በላይ በያይቆብ ዘንድ ትፈቀር የነበረቻው እርሷ እንደሆነችም መመልከት ችለናል፡፡ በዘፍጥረት 29:30 ላይ ከሊያ በላይ ያይቆብ ለእርሷ ፍቅር እንደነበረው ይነግረናል፡፡ ግን ለምድን ነው ከእህቷ በላይ እንደሚያፈቅራት እያወቀች የምትቀናው? ራሄል እህቷ ልጅ ስለወለደች ለምን ቅናት አደረባት? ያይቆብ ከምንም በላይ እርሷን አይደል የሚያፈቅረው?

አስታውሱ ቅናት “የመተካት ፍርሃት ነው” ብለን ነበር፡፡ የራሄል ፍራት የነበረው ሊያ ያይቆብ ለእርሷ የነበረውን ፍቅር ቦታ ትወስዳለች የሚል ነበር፡፡ ቅናት ደግሞ ህብረትን ያፈርሳል ምክንያቱም ቅናት የሚመሰረተው በፍርሃት ላይ ስለሆነ ነው፡፡ በቅናት ተነሳስተን የምናደርገው ነገር በሙሉ ምክንያታዊነት ስለማይኖረው ይጠፋል፡፡ የራሄል ፍርሃት የተፈጠረው ሊያ ለያቆይብ ስድስት ወንድ ልጆችን ስለወለደችለት እና እርሷ ደግሞ ምንም ልጅ ስላልሰጠችው ነው፡፡

## ግላዊ ትግበራ

እናንተስ ቀንታችሁ ታውቁ ይሆን?

1. በህይወታችሁ የቅናት ልምምድ አላችሁን? እስኪ ሁኔታውን ሁሉ ወደ ኋላ መለስ ብላችሁ አስታውሱ።

   ______________________________________________

   ______________________________________________

2. ምን ነበር ፍርሃታችሁ? የመተካት ፍርሃታችሁ ምን እንድታደርጉ አድርጓችሁ ነበር?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

   ______________________________________________

3. ሚቀና ልብ እንደነበራችሁ ለማመን ትቸገራላችሁ? በስራ ወይንም በተለያየ ነገር አብራችሁ ያለው ሰው ይተካኛል ብላችሁ ትሰጋላችሁ?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

## ፀሎት

እግዚአብሔር አምላክ ሆይ በሌሎች ሰዎች መልክ፣ ቁመና፣ ሃብት፣ ትዳር፣ እና መልካም ነገር ብዙ ጊዜ ስቀና እራሴን አግኝቼዋለሁ። ከዚህም የተነሳ በፍርሃት እና ቦታ አጣለው በሚል ስጋት ብዙ ስህተቶችን ፈጽሚያለው። ሰዎችም ለማማት በሌሉበት ሁሉ ስማቸውን አጥፍቻለው። እባክህ አሁን በደሌን ሁሉ ለአንተ እናዘዛለው እና ይቅር በለኝ።

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________።

# ክፍል ስድስት

# የያቦቅን ወንዝ መሻገር

# ዘፍጥረት 32 እና 33 — ያይቆብ ከእግዚአብሔር ጋር ታገለ

---

**አጠቃላይ ምልከታ**

መግቢያ

ክፍል ስድስት 6:  ዘፍጥረት 32 እና 33

- ያይቆብ ዔሳውን ሊገናኝ ተዘጋጀ
- ያይቆብ ጓሁን ሁሉ ያቦቅን አሻገረ
- ያይቆብ አዲስ ስም አገኘ
- ወንድማማቾቹ አንድ ሆኑ
- የያይቆብ እና ኤሳው ውህደት

# ክፍል 1

# መግቢያ

ያይቆብ እና ዔሳው ከተለያዩ በኋላ ዔሳው ምን ሆኖ ይሆን? ዝም ብሎ ጠፋ ማለት ነው? በእርሱ እና በያይቆብ መካከል ምን ተፈጠረ? እንዲያው አንዴም እንኳን ተገናኝተው ያውቁ ይሆን? እነዚህ ሁለት መንቲያዎች በአቋምም፣ በባህሪይም፣ ሆነ በመልክ የሚለያዩ ናቸው። ያይቆብ ከአታለለ በኋላ እና ዔሳው ሊገድለው ካሰበ በኋላ ህብረታቸው ፈርሷል ። በዚህ ትምህርት ያይቆብ እና ዔሳው ከአመታት በኋላ ሲገናኙ ምንድን እንደተፈጠረ አብረን እንመለከታለን።

# የቤት ስራ

ዘፍጥረት 32:3-21 አንብቡ። ማስታወሻ፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ረጃጅም ክፍሎችን ይሆናል የምናጠናው።

መልመጃ

1. በቁጥር ሶስት መሰረት ያይቆብ ያደረገው የሚጀመሪያው ነገር ምንድን ነው?

   ________________________________________

2. ዔሳው የት ነበር?

   ________________________________________

3. ያይቆብ ለወንድሙ የላከው ሶስት መልዕክት ምን ነበር?

   ሀ.________________________________________

   ________________________________________

   ________________________________________

ለ. በቁጥር ስድስት መሰረት መልዕክተኞቹ ለያይቆብ ምን አሉት?

______________________________________________

4. ለዚህ መልእክት ምላሽ ያይቆብ ምን ምላሽ ነበረው ቁጥር7-8?

______________________________________________

5. አፋጣኙ እቅድ ምንድን ነበር?

______________________________________________

______________________________________________

6. ያይቆብ ወደ እግዚአብሔር ፀለየ። የፀሎቱ ዋና ሃሳብ ምን ነበር ቁጥር 9-12? አራት ነገሮችን ልብ በሉ:

ሀ. እግዚአብሔር ማን ነው (ቁጥር 9)?

______________________________________________

ለ. እርሱስ ማን ነው (ቁጥር 10)?

______________________________________________

ሐ. ምንን ጠየቀ (ቁጥር11)?

______________________________________________

መ. እግዚአብሔርስ ምን ቃል ገባለት (ቁጥር 12)?

______________________________________________

______________________________________________

7. ያይቆብ የላከው ስጦታ ምን ምን ያካተተ ነበር። (ቁጥር 14-15)?

ሀ. ፍየሎች: ______________________________________________

ለ. በጎች: ______________________________________________

ሐ. ግመሎች:

______________________________________________

መ. ላሞች:

______________________________________________

ሠ. አህዮች: ______________________________________________

8. ይህንን ሁሉ እየመራ የወሰደው ማን ነው (ቁጥር 16)?

______________________________________________

9. ኢሳውን ሲያገኙት ምን እንዲሉት ነበር ለአገልጋዮቹ ያይቆብ የነገራቸው (ቁጥር 17-20)?

______________________________________________

______________________________________________::

10. በቁጥር 20 መሰረት የያይቆብ ሃሳብ ምንድን ነበር፡፡ ለምን እንደዚያ አሰበ?

______________________________________________

______________________________________________

ክፍል 2

## ማሰላሰል

መሪነት መምራት ነው፡፡መሪነት ደግሞ መከተል መቻልም ነው፡፡ ያይቆብ የቤቱ አባወራ ነው፡፡ እርሱ የጎሳውም አለቃ ነበር፡፡ አሁን ወንደሙን ለመገናኘት ሲመጣ ከእርሱ ጋር አራት መቶ ሰዎችን ይዞ ነበር የመጣው፡፡ ከእነርሱ መካከል መልክተኛ ያደረገው ማንን ነበር? አገልጋዮቹስ!

1. እንደው ጋዜጠኛ ሆናችሁ ብትላኩ እና ወደ እነ ያይቆብ መንደር ብቅ ብትሉ ለያይቆብ የምታቀርቡለት ጥያቄ ምንድን ነው? ለራሄል እና ለሊያስ ምን ጥያቄ ይኖራችኋል?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

2. በእናንተ አገላለፅ ያይቆብ ምን አይነት ሰው ነው?

______________________________________________

______________________________________________

3. በእዚህ ላይ የተመለከታችኋቸውን ነገሮች ፃፉ?

______________________________________________

______________________________________________

## ግላዊ ትግበራ

1. በህወታችሁ ዘመን መሪ ሆናችሁ ነገር ግን በሌሎች መምራት ችግር ሆኖባችሁ ያውቃል? በዚያ አስቸጋሪ ወቅት ምን አይነት ፍርሃት እና ጭንቀት ይዟችሁ ነበር?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

2. እንዲሁም ደግሞ ሌላ የገጠማችሁን የመሪነት ሁኔታ አስቡት

   ሀ. የጠንካራ አመራር በረከቶች ምን ምን ናቸው?

   ____________________________________________________

   ____________________________________________________

   ለ. የደካማ አመራር ውጤት የሆኑ ውድቀቶችስ ምን ምን ናቸው?

   ____________________________________________________

   ____________________________________________________

## የቤት ስራ

ዘፍጥረት 32:22-32 አንብቡት

## መልመጃ

ያይቆብ ቤተሰቡን እና ንብረቱን ሁሉ የያቦቅን ወንዝ አሻግሮ ለብቻው ከወንዙ ማዶ ቀረ። ምሽቱንም ለብቻው በዚያ አሳለፈ (ዘፍጥረት 32:22-24)

1. በዚያ ምሽት ምን ተፈጠረ (ቁጥር 24-26)?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

2. ያይቆብን አንድ ሲታገለው ያደረ ሰው ነበር። እናም ያ ሰው እግዚአብሔር እንደሆነ ክፍሉ ይናገራል። ያይቆብ ግን ታግሎ አሸነፈው። እናም ያ ሰው ምንድን አደረገ (ቁጥር 25)?

ያይቆብ አሁን በአስጨናቂ ሰዓት ላይ ነው ሚገኘው፡፡ ወንድሙ ወደ እርሱ እየገሰገሰ ነው፡፡ እግዚአብሔርን ምን ነበር የጠየቀው (በቁጥር 26 ላይ)?

3. ሰውየው ግን ቅድሚያ ያይቆብን ስሙ ማን እንደሆነ ጠየቀው፡፡ ከዚያም ከዛሬ ጀምሮ ስምህ ያይቆብ አይባልም አለው፡፡ ከዚያ የሰጠው አዲስ መጠሪያ ስም ማን ይባላል?
4. ይህ አዲስ ስም ለውጥን ይፈጥራል?
5. በቁጥር 29 ላይ እግዚአብሔር ያቆብን እንደባረከው እንመለከታለን፡፡ ያይቆብም ያንን ስፍራ አዲስ ስም ሰጠው፡፡ ስሙንም ________________________ አለው፡፡
6. ትርጉሙ ግን ምን ማለት ነው?
7. የያይቆብ የጭኑ ሽሉዳ መነካትን ተከትሎ በእስራኤል ውስጥ የመጣው አዲስ ባህል ምን ነበር (ቁጥር 32)?

# ክፍል 3

# ግላዊ ትግበራ

በዚህ በዘመናዊው አለም ብዙ እነዚህም የመሰሉ ነገሮች ይሆናሉ፡፡ ልክ እንደተወለዳችሁ በወላጆቻችሁ ስም ይሰጣችኋል፡፡ እስኪ የራሳችሁን ስም አስቡት፣ ምን አልባት ገና

እንደተወለዳችሁ ይሆናል ይህ ስም የወጣላችሁ። ገና ከሆስፒታል ሳትወጡ የልደት ሰርትፊኬታችሁ ላይ ሰፍሮ ሊሆን ይችላል።

1. የተሰጣችሁ ስም ምን ነበር?

   ________________________________________________

2. የስማችሁስ ትርጉም ምንድን ነው?

   __________________________________________________

3. ከእናንተ በፊት በዚያ ስም የሚጠራ ሰው ነበር?

   ________________________________________________

4. ማን ነው ያንን ስም ለእናንተ ለማውጣት ስልጣን ተሰጥቶት እንደነበር የሰየማችሁት?

   ________________________________________________________

5. እናንተስ አንድ ሰው በእናንተ ላይ ስልጣን ኖሮት ስም ሲሰይምላችሁ እና እድሜ ልካችሁን በዚህ ስም ስትጠሩ ምን አይነት ምላሽ አላችሁ? ይህ አዲስ ነገር ነውን? ስማችሁን ቀይራችሁ ታውቃላችሁ? እንደው ስታገቡ ወይንም የትዳር ጓደኛ ስትፈልጉ ስማችሁ አልስማማ ብሉአችሁ ስማችሁን ለመቀየር ተነሳስታችሁ ታውቃላችሁ?

   ________________________________________________________

   ________________________________________________________

6. ስም ማውጣት በአንድ ነገር ላይ ወይንም በአንድ ሰው ላይ ያለንን ስልጣን የሚያሳይ ጉዳይ ነው። ወላጆቻችን የወላጅነት መብት እና ስልጣን ስላላቸው ለእኛ ስም ሰጥተው ሰይመውናል። እግዚአብሔር እንዲሁ በእኛ ላይ ስልጣን ያለው አምላክ ነው። ለዚህም ለያይቆብ አዲስን ስያሜን ሰጥቶታል። እስራኤል እንዲባልም አድርጎታል፤ ይህ ማለት ያይቆብ ስም ብቻ ሳይሆን አዲስ ማንነት አግኝቷል ማለት ነው። ያይቆብም ይህንን ስም ሲቀበል የእግዚአብሔርን አገዛዝ እና ስልጣን እውቅና እየሰጠ ይመስላል። እናንተስ ምን ከዚህ ጋር በተያያዘ ስላሳችሁ ምን ታስባላችሁ? __________________________

   ________________________________________________________

   ________________________________________________________

7. እግዚአብሄር የያይቆብን ስም ቀየረ ለእርሱም ህይወት ሙሉ ሃላፊነቱን ወሰደ። እኛንም የህይወታችንን ሙሉ ሃላፊነትን ለመውሰድ ጥሪ ያቀርብልናል። እንዲሁም ለእርሱ ስልጣን ተገዢ እንድንሆን ይፈልጋል። እርሱ ሊባራካችሁ፤ በህይወታችሁ ላያ ባለስልጣን ሊሆን ጥሪ እያቀረበላችሁ እንደሆነ ስትሰሙ ወደ አዕምሮአችሁ ምን አይነት

ሃሳብ ይመጣል?

______________________________________________

______________________________________________

**ፀሎት**

ጌታ ሆይ አንተ ሙሉ በሙሉ በህይወቴ ላይ ስልጣን እንዲኖርህ ለእኔ ጥሪ ማድረግህ አልገባኝም ነበር። አሁን ግን የገባኝ ነገር ህይወቴን እኔ መቀየር እንደማልችል እና አንተ ግን ልትቀይረኝ እንደምትችል ነው። ልክ እንደያይቆብ ከአልባረከኝ አልለቅህም የሚል ልብን ስጠኝ። ለእኔ ስለአለህ ዘላለማዊ ፍቅር አመሰግንሃለሁ።

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

# ክፍል 4

# የቤት ስራ

ዘፍጥት 33:1-17 ውስጥ ያለውን ክፍል አንብቡት።

## መልመጃ

አሁን በያይቆብ ህይወት ውስጥ ለውጥ መጥቷል። አስተውሉ ወንድሙ ከ400 ሰዎች ጋር መምጣቱን ተመልክቷል። እርሱ ደግሞ ቤተሰቡን ትናንሾቹን በማስቀደም እና ትልልቆቹን በማስከተል በሁለት ቦታ አሰልፎአቸዋል። በመጀመሪያ የሚስቶቹን አገልጋዮችና ልጆቻቸውን፤ ከዚያም ሊያን በመጨረሻም የሚወዳትን ራሄልን እና ዮሴፍን አሰለፋቸው።

1. ቁጥር 3 ምን ይላል?

______________________________________________

______________________________________________

ያይቆብ ቀድሞ ሄደ። ቅድሚያውን በመውሰድ መሬት ላይ በመደፋት ራሱን አዋረደ። ዔሳው ወንድሙን ሲመለከት የሰጠው ምላሽ ምን ነበር?

________________________________________________

________________________________________________

ዔሳው ወደ ያይቆብ ሮጠ፤ አቀፈው፤ ሳመው፤ ከዚያም ሁለቱም ተላቀሱ። በቦታው ተገኝታችሁ ሁኔታውን ለመመልከት አልተመኛችሁም። እንዴት ያለ ደስታ ነው! ከቁጥር 5-7 ዔሳው ከያይቆብ ቤተሰብ ጋር ተዋውቋል። ዔሳው ዓይኑንም አነሣና ________________ _________________________እንዲህም አለ ___________________________________? እርሱም________________________ ናቸው አለ።

2. ያይቆብ ልጆቹ ___________________________________ እንደሆኑ ተናገረ።
3. በቁጥር 8 ላይ ዔሳው ለጠየቀው ጥያቄ ያይቆብ ምን ምላሽ ሰጠው? ___________

   ________________________________________________

   ________________________________________________

   ____________

4. በሁለቱ ወንድማማቾች መካከል የሚገርም መገባበዝ ነበር። በቁጥር 9 በመጀመሪያ ዔሳው የያይቆብን ስጦታ አልቀበልም። ምን ብሎ ተናገረ?

   ________________________________________________

   ________________________________________________

5. ያይቆብ ግን ግድ አለው። ምን ብሎ ተናገረ?

   ________________________________________________

   ________________________________________________

ያይቆብ ወንድሙ የተቀበለው ከእግዚአብሔር መልካምነት እንደተነሳ መሆኑን ለመግለፅ ፈልጓል። የሚፈልገውን ሁሉ አግኝቷል (ቁጥር 11)። በመጨረሻም ግድ ስላለው ዔሳው ስጦታውን ተቀበለው።

6. ዔሳው ያይቆብን አጅቦት ወደ ወደ ሴይር ምድር መውሰድ ፈልጓል፤ ነገር ግን ያይቆብ የተለየ እቅድ ነበረው። በራሳችሁ አባባል ያይቆብ ለወንድሙ የተናገረውን ፃፉት____________________________________________

   ________________________________________________

7. ዔሳው በመንገዱ የሚያገኙትን ሰዎች ለሰጠው ፈለገ ፤ የያይቆብ ምላሽ ምን ነበር?

________________________________________________

________________________________________________

8. በቁጥር 16 ላይ ዔሳው ተመልሶ ወደ ሴይር (ኤዶም) ምድር ጉዞውን ቀጠለ። ያይቆብስ ምን አደረገ ?

________________________________________________

________________________________________________

እርሱ ከሴይር በተቃራኒው ወደ ሱኮት ቤተሰቡንና እንስሳቱን ይዞ ተጓዘ። በዚያም መኖር ጀመረ።

# ማሰላሰል

ዔሳው ወደ እርሱ ሮጦ በመምጣት አቅፎት፤ ከሳመው በኋላ በመዋኀዳቸው ምክንያት በደስታ ሲያለቅስ ያይቆብ የሚሰማውን እረፍት አስቡት። የወንድሙን ቁጣ ለማብረድ የተላከው ስጦታ አስፈላጊ አልነበረም ነገር ግን ፊት ለፊት በመተያየታቸው ምክንያት ስጦታን ተቀያየሩ። እነዚህ ወንድማማቾች የቤተሰቡ፤ የይስሐቅና የርብቃ ብቸኛ ልጆች ናቸው።

የሚገርመው ነገር ያይቆብ ወንድሙን ተከትሎ አልሄደም ነገር ግን እግዚአብሄር ለአንደ እና ለዘርህ ርስት አድርጌ እሰጣለሁ ብሎ ምድር በእምነት ተጓዘ።

# የግል ትግበራ

በወንድማማቾቹ መካከል እርቅ ተከናውኗል። በህይወትህ ውስጥ ችግር ያለበትን ግንኙነታችሁ እንዲስተካከል የምትፈልገው ሰው አለ? የተነገረ ቃል ወይንም ድርጊት ሰውን ሊጎዳ ይችላል?

________________________________________________

እግዚአብሄር ለያይቆብ ምህረቱን አብዝቶለት ከወንድሙ ጋር አስታረቀው። በተመሳሳይ መልኩ የአንተንም ህይወት የተበላሸ ነገር ከአለ ሊያስተካክለው ይችላል።

# ፀሎት

ጌታ አምላኬ ያለኝን ሁሉ ነገር አንተ በልግስና የሰጠኸን ነው። ሁሉም ለእኔ የተገቡ አይደሉም። አንዳንድ ጊዜ ተጨማሪ እደሚያስፈልገኝ አስባለሁ። አልፎ አልፎ ተጨማሪ ነገርን

እፈልጋለሁ ግን አንተን የማመሰግነው ከአንተ እንደተቀበልኳቸው ስረዳ ነው። እኔ የበደልኳቸውን ሰዎች ግለጥልኝ። የበደልኳቸውን ይቅርታ የምጠይቅበት ብርታት ስጠኝ። ከሰዎች ጋር የተበላሸውን ግንኙነቴን እንደምታድሰው አምንሃለሁ። አንተ የምትወድደን እና እርስ በእርሳችን በሰላም መኖር እንደምንችል ማድረግ የምትችል ነህ

______________________________________________________________

______________________________________________________________

# የግል ትግበራ

የራሳችሁን ቤተሰብ እስኪ መለስ ብላችሁ አስቡት። ቤተሰቦቻችሁ በጋራ ሲኖሩ ዋጋ የሚሰጡት እና በትክክል የሚከታተሉት ነገር ምንድን ነበር። ከዚያ በኋላ ጎረቤቶቻችሁን አስቡ እንዴት በጋራ እንደሚኖሩ ተመልከቱ።

ትንቢተ ሰፎንያስ ምእራፍ 3፡ ቁትር 17 ላይ ያለውን ክፍል አንብቡት እና ጻፉት። ክፍሉ እንዱህ ይላል።

______________________________________________________________

______________________________________________________________

## የቃል ጥናት

ሰፎንያስ 3:17 በጣም መልካም ከሆኑ እና በቃል ልንይዛቸው ከሚገቡ ጥቅሶች መካከል አንዱ ነው። እናም ይህንን ክፍል በቃላችሁ ለማጥናት ሙከራ አድርጉ።

## ፀሎት

እግዚአብሔር ሆይ አንተ ደግ አባት ነህ። ሁልጊዜ ልጆችህ ስለምትወደን እናመሰግንሃለን። ጌታ ሆይ አንተ እንደምትወደን እኛም ደግሞ አንተን እንድንወድህ እርዳን።

እግዚአብሔር ሆይ ኃጢአትን እና አለማዊ ምኞትን አሸንፈን ለአንተ እየታዘዝን እንድንኖር የአንተ እርዳታ እና ጸጋ ይብዛልን።

## ክፍል 5

## ትምህርት

እስከ አሁን ድረስ በእናቱ እርዳታ ታላቅ ወንድሙን በማታለል ብክሩናውን እንዲሁም አባቱን በማታለል በረከትን ስለተቀበለው ያይቆብ አይተናል። ከዔሳው በመሸሽ ወደካራን እንደሄደም ተመልክተናል። በአጎቱ ላባ ከተታለለ በኂላ የላባ ሁለት ልጆች እንዳገባቸው አጥንተናል። ቀጥለንም ስለ 12 ልጆቸሀ እና ከእግዚአብሄር ጋር ከተገናኘ በኂላ በሁለቱ ወንድማማቾች መካከል ሰላም እንደሰፈነ አውቀናል።

በዘፍጥረት 35 ያይቆብ ከዔሳው ተለይቶ እግዚአብሄር በህልሙ ወደ ተናገረው ወደ ቤቴል ( ዘፍጥረት 28:10-15) ሄደ። እግዚአብሄር በድጋሚ ተገልጦለት ስሙን ቀይሮ እስራኤል አለው ( 35:9-13)። በዚህ ክፍል ውስጥ ራሄል ቢኒያምን ስትወልድ እንደሞተች እንመለከታለን። ቢኒያም ከያይቆብ 12 ልጆች መካከል የመጨረሻው ነበር። እርሱና ወንድሙ ዮሴፍ የራሄል ልጆች ስለሆኑ በያይቆብ በጣም ይወደዱ ነበር። በቁጥር 27-29 ላይ ያይቆብ ወደ አባቱ ምድርውደ ኬብሮን ተመለሰ። ይስሐቅ 180 አመታትን ከኖረ በኂላ ሲሞት ዔሳው እና ያይቆብ ቀበሩት።

ምዕራፍ 36 ስለዔሳው ትውልድ ይገልፃል። ለሁለቱ ወንድማማቾች እንስሳት የሚበቃ ሳርና ውሃ ባለመኖሩ ምክንያት ዔሳው እንስሳቱን ይዞ ወደ ተራራማው ሴይር አገር ወደ ኤዶም ሄደ የኤዶምም አባት ሆነ። ዔሳው የአባቱን የይስሐቅን አምላክ በመተው ከነዓናዊያንን እና የኪጣውያን ልጆችን አገባ። እነዚህ በእግዚአብሄር የተመረጡ ህዝቦች አይደሉም።

ከዚያ በኂላ ያይቆብና ዔሳው በድጋሚ ተገናኝተው ይሆን? መፅሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጥያቄ የሚናገረን ምንም ነገር የለም። አንድ የምናውቀው ነገር መፅሐፍ ቅዱስ ስለዔሳው ጥሩ

ነገር እንዳልዘገበ ነው፡፡ እስራኤላዊያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ሊገቡ ሲመጡ ኤዶማዊያን ችግር እደፈጠሩባቸው ተፅፎ እናገኛለን፡፡ ኤዶማዊያን የሚታወቁት ሀሰተኛ አማልክትን በማምለካቸው ነው፡፡

አንድ የሚገርም ነገር አብረሐም ሁለት ልች ነበሩት፤ ታላቅዬው ከአባቱ አምላክ ተለይቶ ወደ ግብፅ ሄደ፤ ሁለተኛው ልጁ ይስሐቅ ግን ለአባቱ የተገባለትን የተስፋ ቃል ይዞ ቀጠለ፡፡ ይስሐቅም ሁለት ልጆች አሉት፡፡ ታላቅዬው የአባቱን አምላ ትቶ ወደ ኤዶም አገር ሄደ ሌላኛው ልጅ ያይቆብ ግን ወደ አባቱ አገር ወደ ካራን በመመለስ ለአያቱ እና ለአባቱ ከእግዚአብሄር የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል ይዞ ቀጠል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ነገር ከአንድ ቤተሰብ አንደኛው የአባቱን አምላክ ሲከተል ሌላው ሲተወው ነው፡፡

## የግል ትግበራ

ስለራሳችሁን ቤተሰብ አንዴ አስቡና ስለወላጆቻችሁ እሴትና እምነት ያላችሁን አመለካከት ምን ይመስላል፡፡ አንድ መታወቅ ያለበት ነገር የወላጆች ሃይማኖት ትክክለኛ አምላክን የሚያመልክ መሆኑን ነው፡፡ ከዚያም እያንዳንዱ ሰው በትክክለኛ መንገድ ላይ መሆኑን መፈተሽ አለበት፡፡ ወላጆች ሆነ ልጆች ፣ ቀጣሪ ሆነ ተቀጣሪ፤ ተማሪ ሆነ አስተማሪ ሁሉም ኃጢአተኞች እና በኃጢአተኛ አለም ውስጥ የሚኖሩ ናቸው፡፡ አሁንም ወደ እርሱ እንድንመጣና እርሱን እንድንከተል ኢየሱስ ክርስቶስ ጥሪን ያቀርብልናል፡፡

እግዚአብሄርን በፍፁም ልባችሁ ከማምለክ እና ከመከተል ልባችሁ ሸፍቶ ያውቃል? ሁልጊዜ የሚወዳችሁ እና ልጁ ሊያደርጋችሁ ለሚጠራችሁ አምላክ ለእግዚአብሄር ምላሽ ሰጥታችሁ ታውቃላችሁ? ምድራዊ ወላጆቻችሁ ሊያደርጉት የማይችሉትን እግዚአብሄር ሰማያዊው አባታችሁ ሊሆን ጥሪን ያቀርባል፡፡ ሶፎኒያስ 3:17 እርሱ በእኛ እደሚደሰት ይናገራል፡፡ ጥቅሱን ፃፉት

________________________________________

________________________________________

## ማሰላሰል

ሶፎኒያስ 3:17 ሁልጊዜ ልታስታውሱት የሚገባ ጥቅስ ነው፡፡ በልጁ ስሚደሰት አባት የሚናገር ነው፡፡ አሁንም ጥቅሱን ለየት ባለ ማስታወሻ ላይ ፃፉትና ከእናንተ ጋር እስሚዋሀድ ድረስ ደጋግማችሁ በየእለቱ በቃላችሁ ተናገሩት፡፡

## ፀሎት

አምላካችን ሆይ አንተ አባታችን ልትሆነን ፈቃድህ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ኃጢአተኛ የሆኑ ምድራዊ አባቶቻችንን በመመልከት አባትነትን በተሳሳተ መንገድ ተረድተነዋል፡፡ ህይወቴን የሞላውን ፍቅርህን ማየት እንድችል አይኖቼን ክፈት፡፡ የአንተ ፍቅር ደግሞ ይህንን ማድረግ ይችላል፡፡ የአንተ ፍቅር መረዳት የማልችለውን እንድረዳ ያደርጋል፡፡ የአንተ ፍቅር እኔን ከማንኛውም ጥቃት ይጠብቃል፡፡ በእኔ ደስ ይበልህ፡፡ እኔ ደግሞ ኃጢአተኛ ስለሆንኩኝ ይህንን ልረዳ አልቻኩኝም፡፡ በፍቅርህ አረጋጋኝ፤ በደስታህ ሙላኝ፡፡ እኔ የሚያስጨንቀኝን ሁሉ በአንተ ላይ እጥላለሁ፡፡

# ክለሳ

# የእግዚአብሄር ታማኝነት ፤ የእኛ ተስፋ



**ክለሳ**

ይህ ክፍል የታቀደው የእናንተን ስለ ብሉይ ኪዳን ዋና ዋና ሰዎች ይሰሐቅ፤ ርብቃ፤ ዔሳው እና ያይቆብ ያላችሁን እውቀት ለማዳበር ነው።

በራስህ አገላለፅ የእያንዳንዱን ሰው ባህሪ በአጭሩ አብራራ/ሪ:

ሀ. ይስሐቅ:

________________________________________________

________________________________________________

ለ. ርብቃ:

______________________________________________

______________________________________________

ሐ. ዔሳው:

______________________________________________

______________________________________________

መ. ያይቆብ:

______________________________________________

______________________________________________

በዘመኑ ቋንቋ ይህንን ቤተሰብ አንድነቱን መጠበቅ ያቃተው እና ተግባሩን መፈፀም እንዳልቻለ አድርገን ልንቆጥረው እንችላለን። ምንም እንኳን እንደ ሰው ድካም ቢኖርባቸውም ለእነርሱና ለያይቆብ ልጆች የነበረውን የእግዚአብሄርን ታማኝነት ምን እንደነበር አብራራ/ሪ:

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

ለዚህ ቤተሰብ የእግዚብሄር መልካምነት በእነርሱ ባህሪይ የተወሰነ አልነበረም። የሚያደርጉት ሁሉ ነገር እርሱ እነርሱን እንዳይወዳቸው አላደረገም። ከዚህ ጥናት እግዚአብሄርንን በበለጠ እንድንታመነው የሚያደርግ ነገር ምን ተማራችሁ (ዮሐንስ 3:33) እና ( ዮሐንስ 3:16)?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

____________________________በርካታ የሰዎችን ስም እና የቦታ ስሞችን ተምራችኋል። የሚከቱሉተን አዛምዷቸው።

ሀ. ካራን 1. የመጀመሪያ ልጅ የሚወርሰው

ለ. ላባ 2. የእስራኤል ቀደምት አባቶች

| | |
|---|---|
| ሐ. ቤቴል | 3. ያይቆብ ህልም ያለመበት |
| መ. አስራት | 4. ኤዶም |
| ሠ. በረከት | 5. የያይቆብ አዲሱ ስም |
| ረ. ብኩርና | 6. እግዚአብሄር ለያይቆብ ከሰጠው አንድ አስረኛው |
| ሰ. አባቶች | 7. የልጅን ህይወት የሚመራ የአባት ቃል |
| ሸ. እስራኤል | 8. የርብቃ ወንድም |

እንኳን ደስ አላችሁ! የእግዚአብሄር ታማኝነት የእኛ ተስፋ የሚለውን ጥናት አጠናቅቃችኋል፡፡ ከብሉይ ኪዳ ታሪኮች ጋር በበለጠ እየተዋወቃችሁ ነው፡፡ በእነዚህ ሰዎች ህይወት ውስጥ የእግዚአብሄርን ፍቅር እና ከመረጣቸው ሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት አይተናል፡፡ ከእኛም ጋር የፍቅር ህብረትን ማድረግን ይፈልጋል፡፡ ግብዣው ለእኔና ለእናንተም ፡፡ የእርሱ ግብዣ አምላችን አድርገን እንድንቀበለው እና ልጁን እየሱስ ክርስቶስን አዳኛችን እና የድነት ተስፋችን አድርገን እንድንቀበለው ነው፡፡ በጥናታችሁ ቀጥሉበት፡፡ ጥናታችን በቀጠላችሁ መጠን ብዙ የምስራች ቃል ታገኛላችሁ፡፡

## ፀሎት

ጌታ እግዚአብሄር ሆይ አንተ አባቴ ነህ፡፡ ቃልህ በአጠናሁ ቁጥር ራስህን ግለጥልኝ፡፡ ከዚህ በፊት አንተ የመረጥካቸውን ሰዎች ታሪክ ሳጠና ልቤን ክፈትና ተናገረኝ፡፡ ምንም እንኳን ያለፈው ታሪኬ ጥሩ ባይሆን በእኔ ልትጠቀም እንደመረጥከኝ አስተውል ዘንድ እርዳኝ፡፡ ህይወቴን በተስፋ እና በአላማ ሙላው፡፡ አንተ በባረከኝ መጠን ለሌሎች በረከት እሆን ዘንድ እርዳኝ፡፡ የአንተ ምኞት የእኔ ይሁን ምክያቱም ታማኝነትህ ስለበዛልኝ ነው፡፡

______________________________________________

______________________________________________